# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 298 ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

## «በምክክር መድረኩ የሚሳተፉ ሁሉ እኔ ምን አተርፋለሁ ሳይሆን ኢትዮጵያ ምን ታተርፋለች የሚለውን ይዘው መምጣት አለባቸው»

-ዶክተር ዐቢይ አሕመድ
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

ገጽ 4

## «ሕወሓት በጦርነቱ ከተከሰተው ውድመት ትምህርት በመውሰድ ለሰላም ውይይቱ ዝግጁ መሆን አለበት»

-ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ



**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት ከዚህ በፊት በተደረገው ጦርነት ከተከሰተው ውድመት ትምህርት በመውሰድ ለሰላም ውይይቱ ዝግጁ መሆን እንዳለበት ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ አሳሰበ።

ሻለቃ ኃይሌ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጠው አስተያየት እንደገለጸው፤ የአገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ያደረጉት ጥረት በተለይ በሕወሓት በኩል አዎንታዊ ምላሽ ባለማግኘቱ በተደረገው ጦርነት አስከፊ ውድመት ተከስቷል።

«ሕወሓት በጦርነቱ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በክልሉ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ እየተቀረፉ መሆኑ ተገለጸ

**አምሳሉ ፈለቀ**

ሐዋሳ፡- በሲዳማ ክልል ከዚህ ቀደም ስር ሰድደው የቆዩና በሕዝቡ ዘንድ ጥያቄ ሲያስነሱ የቆዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት እየተቀረፈ መሆኑን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ አስታወቁ።

የሲዳማ ሕዝብ ለበርካታ ዓመታት የእኩልነትና የመልማት ጥያቄ ሲያነሳ ቆይቶ በአገሪቱ በመጣው የለውጥ ሥርዓትና በሕገ መንግሥቱ መሠረት ምላሽ አግኝቷል ያሉት አቶ ደስታ፤ ከሕዝቡ የመልማት ፍላጎት ጋር ተያይዞ ይነሱ የነበሩት የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ እየተደረገ ነው ብለዋል።

በዚህም ከዚህ ቀደም ለዘመናት ስር ሰድደው የቆዩት የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ እያገኙ የሕዝቡን ፍላጎት በመለየት እየተሠራ ሲሆን፤ በቀጣይም የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የማይነሳበት ክልል እንዲሆን ይሠራልም ነው ያሉት።



የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምሥረታ 2ኛ ዓመት ትናንት በይፋ የተከበረ ሲሆን ይህ ቀን በሲዳማ ሕዝብ ዘንድ የድል ቀን ሆኖ በየዓመቱ እንደሚበከር ተናግረዋል።

የክልሉ ሕዝብ የእኩልነትና የመልማት ጥያቄ ደረጃ በደረጃ ምላሽ እያገኘ መምጣቱን የጠቆሙት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የክልሉ መንግሥት ከተመሠረተ በኋላም ባለፉት ሁለት ዓመታት በተለያዩ ዘርፎች አመርቂና ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማስመዝገብ መቻሉንም ተናግረዋል።

ርዕሰ መስተዳድሩ እንዳሉት፤ የሲዳማ ሕዝብ ራሱን በራሱ ለማስተዳደርና ለመልማት ለዘመናት መራራ ትግል ሲያደርግ ቆይቶ ባገኘው ድል ሳይኩራራ በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ ፊቱን ወደ ልማት አዙሯል።

የሕዝቡ ፖለቲካዊ ጥያቄ ምላሽ ካገኘበት ማግስት አንስቶም በክልሉ የተረጋጋና አስተማማኝ ሠላም የሠፈነበት ሁኔታ በመፈጠሩ በአሁኑ ወቅት ለቱሪዝም፣ ለኢንቨስትመንት እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች በበርካቶች

በክልሉ የመልካም... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## «በኢትዮጵያ ስሚታየው የሰላም መደፍረስ ዋነኛው መንስኤ ወያኔ ነው»

-ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
የኢፌዴሪ ፖሊሲ ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

ገጽ 4
















# ከልጅነት ወደ ወጣትነት መሻገሪያው ፈተና

ዳግማዊት ግርማ

ልጅነት የማይመለስ ትዝታ የማይደገም የለጋነት ዘመን የማደግ ትናንት ነው። እንደ ልጅነት ያለም አልፎ ሲታይ በደስታ ልብን እያወዛ መንፈስን እያደሰ ሳይዳበስ የሚያልፍ ውብ የትዝታ ዘመን የለም። ያ የልጅነት ጊዜ ደግነት የሞላበት፤ ታዛዥነት የከበበው ውብ ዘመን ነው። በመውደቅ እና በመነሳት በብዙ ድካም ልብ በርትቶ አጥንት ጠንክሮ አዕምሮ በስሎ ያንን የቅንነት ዘመን እያሰበ ያልተደሰተ ያለ ቢመለስም ምናለ ደግሞ ቢገኝ ብሎ ያልተመኘ ሰው የለም።

የልጅነት ዘመን በናፍቆት የሚታወስ የዕድሜ የዋህ ወራት አካል፤ ተፈጥሮ እንደሰጠን ያለ ምንም ያልተቀባባ ያልተኳለ የዕድሜ ጅማሮ ነው። በልጆች ልጅነት በትንሿ ልባቸው በደማቁ የተሳለች የልጅነት ጌጥ አንድ አካል ነበረች፤ ትምህርት ቤት።

ልጅ ከልጅነቱ እኩል የሚያውቀው ወላጅ እናቱን እና የአደራ እናቱን ትምህርት ቤቱን ነው። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ብዙ ማፈር እልፍ አለማወቅ አልፏል። ሰው ሰው መሆንን የሚማርበት ከትናንቱ ለተሻለ ዛሬ የሚተጋበት ከእናቱ እቅፍ እንደወጣ ቀድሞ ያቀፈው ትምህርት ቤቱ ነው፤ አንገቱ ስር የሸጎጠው የሰርክ ጸሎቱ ከአስኳላው ደጃፍ መገኘት ነው።


በእውቀት ጅማሮ ዕድሜ ላይ ሁለት ዓይነት ሕፃናት አሉ፤ ትምህርት ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርግ ሆኖ ያደገና ከአካላዊ አቅሙም ከጭንቅላቱ የማሰብ መጠን በላይ በመሥራት የማጥኛ ጊዜውን ያልተጠቀመ።

ከማደግ እኩል እውቀትም ያድጋል፤ ልጅ ትምህርት ቤት ውስጥ ፊደል ብቻ አይቆጥርም ፍቅርን፣ ክብርን፣ ለዛን ጨዋታን ቁምነገርንም ጭምር እንጂ። ከመምህራን ከንፈር እልፍ ቁጣዎች ብዙ ምክሮች ይሄን ያህላል የማይባሉ የርህራሄና እዝነት ቃላት ተደምጠዋል።

የዚህ ሁሉ ግሳፄና ፍቅር ውጤት ደግሞ በፈተናዎች ወንፊትነት ነው ግርድፉ ከብስሉ የሚለየው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ለዚህ ነው የጋዜጠኞች ቡድኑን በማሰማራት ትናንትና በመላው አዲስ አበባ መሰጠት በጀመረው የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ


ፎቶ፡- አዮብ ተፈሪ
ሲፈን ካሳሁን


አቶ ተስፋዬ ካሳሁን


አቶ ደበሳ ከበደ

ፈተናን ለመታዘብ በ1949 ዓ.ም በተመሠረተው መድኃኒዓለም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ታድሞ የነበረው።

ትምህርት ቤቱ ስንደርስ ሰዓቱ ለተማሪዎች ከፈተና መውጫቸው ነበርና በተማሪዎች የተወረረ ጊቢ ተመለከትን፤ ወደ ጊቢው ገብተን ጥጋችንን እንደያዝን በምልከታችን ውስጥ የፈተና መልስ ለመመሳከር ከጓደኞቹ ጋር ክርክር የያዘ፣ ምናለ መልሼው ቢሆን የሚል የፀፀት ጥላ ፊቱ ላይ ያጠላበት፣ የፈተና ድንጋጤ የሚስተዋልበት ላባም ፊቱን ደጋግሞ የሚጠራርግ ብቻ ብዙ ዓይነት ፊቶች አፋቸውን ከፍተው ተቀበሉን።

የመድኃኒዓለም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህሩ አቶ ደበሳ ከበደ በፈገግታ የተሞላ ፊታቸውን አሳይተውን ወደ ቢሯቸው እንድንገባ ጋበዙን። በዚያውም ትምህርት ቤታቸው በየአመቱ ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ለመፈተን የሚመጡበት እንደሆነ አወጉን። በአሁኑም አመት ከአምስት ከግልና ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች የመጡ በቀንና በማታ የሚማሩ 589 ተማሪዎች ለፈተናው መቀመጣቸውን ገለፁልን።

ከንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲገቡ እንደነበር አቶ ደበላ ነግረውናል። ተማሪዎችን ከፈተና መፈተኛ ሰዓታቸው ከሰላሳ ደቂቃ በፊት ወደ ክፍሎቻቸው ገብተው ጊዜ ወስደው ራሳቸውን አረጋግተው መፈተን መጀመራቸውንም ገልጸውልናል።

የመድኃኒዓለም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንዳይኮራረጁ ተማሪዎቹ ላይ መሠራቱንና ኩረጃ ገዳይ መሆኑን በማወቅ ላይ የተመሠረተ እውቀት ለተማሪዎች ሲመግብ መከረሙን ነግረውን ተማሪዎቹን በኩረጃ እንደማይጠረጥሯቸውም ነግረውናል።

የመድኃኒዓለም ፈተና ጣቢያ ኃላፊ የሆኑት አቶ ተስፋዬ ካሳሁንም የፈተና ሂደቱን በሚመለከት አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።

ፈታኞችና ተፈታኝና ተቆጣጣሪዎች ሥራቸውን በአግባቡ መከወናቸውን የገለፁት አቶ ካሳሁን በፈተናው ሂደት ወቅት እንዲሁም ከመጀመሩ በፊት የጣለው ዝናብ በሥራቸው ላይ ትንሽ መንገዳገድ ፈጥሮባቸው እንደነበርም ተናግረዋል።

በፈተና ሂደቱ ላይ የተሳተፉ ፈታኞች ምንም ዓይነት ችግር አለማየታቸውን ያወጉን አቶ ደበላ በመፈተኛ ጣቢያው አምስት ሱፐርቫይዘሮችና ሁለት አጋዦች እንዲሁም ሃያ የፀጥታ አካላት ተሳትፎ ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

ወደፊት ሕግ የመማር ሀሳብ እንዳላት ያወጋችን የስምተኛ ክፍል ተማሪዋ ሲፈን ካሳሁን በበኩሏ የፈተና ሂደቱ ሰላማዊና ምቹ እንደነበር ገልፃልናለች።

ፈተናው ጥሩና ለማለፍ ተስፋ የጣለችበት እንደሆነ ያጫወተችን ሲፈን በትናንትናው ዕለት አማርኛና እንግሊዝኛ ፈተናዎችን ያለምንም ችግር መፈተኗን ተናግራለች።

ትናንትና በአዲስ አበባ በተጀመረው የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ (ስምንተኛ ክፍል) መልቀቂያ ፈተና 71 ሺህ 832 የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በ179 የፈተና ጣቢያዎች ለፈተና መቀመጣቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው አቶ አበበ ቸርነት ገልጸዋል።

ጅማሮውን ትናንት ያደረገውና ፈተና ዛሬ ሁለተኛ ቀኑ ሲሆን፣ ለሦስት ቀናት ቆይታውን በማድረግ በነገው ዕለት ማሳረጊያው ይሆናል። በፈተናው 1800 ፈታኞችና 450 ሱፐርቫይዘሮች ተሳታፊ እንደሆኑም ከኃላፊው መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

# ኮሚሽኑ የሽጦ ማምረት አሠራርን እንደሚያበረታታ ገለጸ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን የግብርና ምርቶችንና የሸቀጦችን ዋጋ ንረት በዘላቂነት ለማረጋጋት አምራች አርሶ አደሮች የሽጦ ማምረት አሠራርን እንደመፍትሄ ተጠቅመው በግልና በኩታገጠም እንዲያመርቱ በማበረታታት ሁኔታዎችን ሊያመቻች መሆኑን ገለጸ።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ አብዲ ዑመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በገበያ ተፈጥሮ ዋጋን የሚወስነው አምራቹ ሆኖ እያለ አሁን ዋጋ እየተመነ ያለው ሌላ አካል ነው። ይህ ደግሞ አምራቹን ኃይል የመደራደር አቅም እንዳይኖረው አድርጓል። በዚህም ምክንያት ኮሚሽኑ ሽጦ ማምረት የሚል አሠራር በመቅረፅ አምራቾች እንዲያመርቱ ሊደረግ ነው።

የሽጦ ማምረት አሠራር አምራች አርሶ አደሮች በቡድን ወይም በግል በመሆን ከምርት ገዢ ተቋማት ጋር አስቀድመው በመዋዋል እና የድጋፍ ገንዘብ በመቀበል አምርተው የሚያስረክቡበት አሠራር ነው።


አቶ አብዲ ዑመድ

አሠራሩ የአምራቹን የመደራደር አቅም ከመጨመሩም ባሻገር ከገበያ ላይ ከማኅበረሰቡ እኩል ተሻምተው በገፍ የሚገዙ ድርጅቶችን በማስቀረት ገበያውን የሚያረጋጋ እንደሆነ ምክትል ኮሚሽነሩ ገልፀዋል።

ማረሚያ ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ሆስፒታሎች እና አደጋ ስጋትን የመሳሰሉ ትላልቅ ተቋማት ከአምራቹ ጋር ምርቱ ከመመረቱ አስቀድሞ እንዲመረት የሚፈልጉትን በመነጋገር ተቋማቱ በየጊዜው ከክፍት ገበያ ምርቶችን እየገዙ የሚፈጥሩትን እጥረት ለማስወገድ ይረዳል ሲሉም አክለዋል።

በተጨማሪም ይህ አሠራር ዕሴት ሳይጨምር ከፍተኛ የትርፍ ህዳግ የሚወስደውን አካል (ደላላ) ቆርጦ የሚጥል እንደሆነ ያብራሩት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ትላልቆቹ የግብርና አቅርቦት ፈላጊ ተቋማት የራሳቸውን ቋሚ ፍላጎት የሚያውቁ በመሆናቸው አስቀድመው ከአምራች ጋር እንዲነጋገሩና ቀብድ እንዲከፍሉ በማድረግ ፍላጎታቸውን ከአቅራቢ ከሚገኝ ቦታ እንዲያገኙ የሚያስችል አሠራር እንደሆነ ጠቅሰዋል።

የአሠራሩ ዋና ዓላማም አምራቹ የገበያ ስጋት ሳይኖርባቸው አምርቶ፤ ገዢውም በአስተማማኝ ሁኔታ ገዝቶ እንዲሁም ከመካከል ላይ እሴት ሳይጨምር ዋጋን የሚያንረው አካል (ደላላ) ተቆርጦ እንዲወጣ በማድረግ ዋጋን ማረጋጋት ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል የዋጋ ንረት በተጠቀሰው መንገድ ብቻ መከላከል የሚቻል ባለመሆኑ ሌሎች ዋጋን የማረጋጋት ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ተጠቁሟል። የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሚና የበለጠ ጎልቶ የሚታየው የቀውስ ጊዜ ሲከሰት እንደሆነ የጠቆሙት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ የዩክሬንና የራሽያ ጦርነት በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይ በግብርና ምርቶች ላይ እና በተያያዥ ነገሮች ላይ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ንረትን ማስከተሉን ተከትሎ ዋጋን ለማረጋጋት በኮሚሽኑ በኩል ተጨማሪ እርምጃዎች እንደሚወሰድ አብራርተዋል።

ማዳበሪያን የመሳሰሉ እና ሌሎች የግብርና ግብዓቶች በከፍተኛ ሁኔታ መናር፤ የነዳጅ ዋጋ መጨመር እና ስንዴና ዘይትን የመሳሰሉ የምግብ ምርቶችም ከራሽያና ዩክሬን ጦርነት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ እጥረት መፈጠር በድምሩ ኢትዮጵያ ላይ በአንድም በሌላም መልኩ ተፅዕኖ ፈጥረዋል ያሉት ኮሚሽነር አብዲ ዋጋዎችን ለማረጋጋትና የአቅርቦቶችን እጥረት ለመፍታት መንግሥት በራሱ የሚያደርገው ጥረት ቢኖርም የኅብረት ሥራ ማኅበራትም ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ አቅርቦቱ ፍትሃዊ እንዲሆን እየሠሩ እንደሆነ ተናግረዋል።

# የነዳጅ ድጎማ ክፍያን ለመፈጸም የሚያስችል መተግበሪያ ይፋ ሆነ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር፣ በኢትዮ-ቴሌኮምና በኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት መካከል የለማውና ብሔራዊ የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ክፍያን ለመፈጸም የሚያስችለው መተግበሪያ ይፋ ሆነ። መተግበሪያውን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ፤ የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬህይወት ታምሩና የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታደሰ ኃይለማርያም የመግባቢያ ሰነዱን ተፈራርመዋል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴርን ወክለው ገለጻ ያደረጉት አቶ አብዱልበሽር ሽምሱ እንደገለጹት፤ ከሐምሌ ወር ጀምሮ ተግባራዊ ለሚደረገው የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ሥርዓት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። ከዚህም መካከል ድጎማ የሚደረግላቸውን ተሽከርካሪዎች መለየትና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማጣራት፣ መዝግቦ መያዝ፣ ተሽከርካሪዎች የድጎማ ተጠቃሚዎች መሆናቸውን የሚገልጽ ስቲከር ማዘጋጀት፣ አሽከርካሪዎች የቴክኖሎጂ መተግበሪያው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማዘጋጀት ከቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መካከል እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል።

የለማው መተግበሪያ በአዳማ፣ አዲስ አበባ፣ ሀዋሳ፣ ወላይታ ሶዶና ባህርዳር ከተሞች ላይ የሙከራ ትግበራ የተከናወነ ሲሆን ውጤታማ መሆኑ ተረጋግጧል ብለዋል።

በታለመለት የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብለው የተመዘገቡት 164 ሺ 345 ተሽከርካሪዎች ተለይተዋል ያሉት አቶ አብዱልበሽር፤ የድጎማ አፈጻጸሙን ለመተግበር አምስት ደረጃዎች የታዩ ሲሆን የተሽከርካሪዎች ዓይነት፣ የሚጓዙት ኪሎ ሜትር፣ የመንገድ ሁኔታ፣ የነዳጅ ዓይነት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑና ከተመዘገቡት ተሽከርካሪዎች 140 ሺ 208 የሚሆኑት በቴሌ ብር መመዝገባቸውንም አብራርተዋል።

ለታለመለት ድጎማ የተመረጡ ተሽከርካሪዎች ሦስት እግር ተሽከርካሪዎች፣ የከተማ አውቶቡሶች፣ ሚዲባሶች፣ ታክሲዎች፣ አገር አቋራጭ አውቶቡሶች፣ ለመንግሥት ሠራተኞች አገልግሎት የሚሰጡ አውቶቡሶች ናቸው። መተግበሪያው ለቁጥጥር የሚመች ሆኖ የለማ ሲሆን በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የሚመራ መሆኑም ተገልጿል።

በአገሪቱ አገልግሎት ከሚሰጡ ማደያዎች ውስጥ 860 የሚሆኑት ማደያዎች እስካሁን ድረስ ተመዝግበው አገልግሎቱን ለመስጠት አስፈላጊውን ስልጠና መውሰዳቸውን ገልጸዋል። ድጎማው ለማኅበረሰቡ እንጂ ለተሽከርካሪ ባለሀብቶች አለመሆኑን ኅብረተሰቡ መገንዘብ አለበት ብለዋል።

በቴሌ ብር እንዴት መፈጸም እንደሚቻል ኢትዮ ቴሌኮምን ወክለው ማብራሪያ የሰጡት አቶ ቸርነት የሻምበል እንዳሉት፤ ክፍያውን በቴሌ ብር ደህንነቱ በተጠበቀና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለመፈጸም ዝግጅት ተደርጓል። ክፍያውን ለመፈጸም የኔትወርክ ጥራቱ 99 ነጥብ 7 በመቶ አቅም አለው።

ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ




የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስትሯ በስምምነት ፊርማው ወቅት እንደገለጹት፣ የበለጸገው የክፍያ መተግበሪያ ሥራን የሚያቃልልና ክፍያውን በቀላሉ ለመክፈል የሚያስችል ነው። አንድ አሽከርካሪ ነዳጅ ቀድቶ ለመጨረስና ክፍያ ለመፈጸም የሚያስችለውና የተፈቀደለት መጠን የመለያ ሥርዓት ያለው በመሆኑ ሥራን የሚያቀላጥፍ ነው።

ሚኒስትሯ ያልተመዘገቡ ማደያዎችና የተሽከርካሪ ባለሀብቶች እንዲመዘገቡም ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን በአገልግሎቱ ለሚፈጠረው ችግር እገዛ ለማግኘት በነፃ የስልክ መስመር 9719 መደወል እንደሚቻል ጠቁመዋል።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬህይወት ታምሩ በበኩላቸው የታለመለትን የነዳጅ ድጎማ ለማስተግበርና በተቀናጀ የቁጥጥር ሥርዓት ለማስተዳደር ኢትዮ ቴሌኮም መተግበሪያውን በአጭር ጊዜ ውስጥ አብልጽጎ ማቅረቡን አስታውቀዋል። የበለጸገው የክፍያ መተግበሪያ በራስ አቅም የለማ ሲሆን ገንዘብንና ጊዜን የሚቆጥብ ዘመኑን የመጠነ ቴክኖሎጂ ነው። ክፍያው የኢትዮ ቴሌኮም የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት በሆነው ቴሌ ብር አማካኝነት የሚፈጸም ሲሆን፤ የድጎማ ሥርዓቱን ሂደት የቀን፣ የሳምንት፣ የወርና የዓመት ሪፖርቶችን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና ለባለድርሻ አካላት በቀላሉ ማቅረብ የሚያስችል ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታደሰ ኃይለማርያም እንደገለጹት፤ የለማው ቴክኖሎጂ በነዳጅ ግብይት ላይ ይደርስ የነበረውን ማጭበርበር የሚቀንስ ነው። በተጨማሪም ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ከሚኒስቴሩ በሚቀርብለት መረጃ በመነሳት የነዳጅ ፍላጎት ለታለመ የነዳጅ ድጎማ የሚሆን በጀት በቴሌ ብር አካውንት በኩል በማቅረብ የድጎማ ሥርዓቱን ቅልጥፍና ያግዛል።

# በዘርፉ ለአገር ውስጥ ባለሙያዎች ዕድል መነፈጉ አገሪቷን ለውጭ ምንዛሪ ብክነት መዳረጉ ተጠቆመ

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሰመራ፡- በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ለሰለጠኑ የአገር ውስጥ ባለሙያዎች ዕድል አለመስጠቱ አገሪቷ ከዘርፉ የምታገኘውን የውጭ ምንዛሬ የውጭ አገራት ባለሙያዎችን በመቅጠር እንድታባክን እያደረጋት መሆኑን የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የሆቴል አስተዳደር ተመራማሪና አማካሪ አቶ ይታሰብ ስዩም ተናገሩ።

አቶ ይታሰብ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ከአሥር ዓመታት በላይ በዘርፉ ልምድ ያላቸውና እስከ ባለአምስት ኮከብ ሆቴሎችን የመምራት አቅም ያላቸው የአገር ውስጥ ባለሙያዎች ቢኖሩም አብዛኞቹ ትላልቅ ሆቴሎች ከውጭ አገራት ባለሙያዎችን እያስመጡ ይቀጥራሉ።

ይህ አካሄድ ዜጎችን የሥራ ዕድል እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ አገሪቷ በዘርፉ የምታገኘውን የውጭ ምንዛሪ የውጭ አገራት ባለሙያዎችን በመቅጠር መልሳ እንድታጣው ያደርጋታል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ለማስቻል በሙያው ለሰለጠኑ የአገር ውስጥ ባለሙያዎች ዕድል ሊሰጣቸው እንደሚገባም አስተያየታቸው ሰጥተዋል።

ኢትዮጵያ ለቱሪዝም ዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠትና ዜጎችም ዘርፉ በሚፈጥረው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ለማድረግ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ አሁን ላይ እስከ 15 በሚደርሱ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች በመጀመሪያ ዲግሪ ባለሙያዎችን እያሰለጠነች ትገኛለች ያሉት ተመራማሪው፤ አብዛኞች ትላልቅ ሆቴሎች ለአገር ውስጥ ባለሙያዎች ዕድሉን በመንፈግ የውጭ አገራት ባለሙያዎችን እየቀጠሩ እንደሚገኙም አስረድተዋል።

እነዚህ ከውጭ አገራት የሚመጡ ባለሙያዎች ከአገር ውስጥ ባለሙያዎች አንጻር እዚህ ግባ የሚባል የተለየ ልምድና ብቃት እንደሌላቸው ጠቅሰው፤ በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰለጥኑ ሙያተኞች ከአሥር ዓመታት በላይ የሥራ ልምድ ያላቸውና እስከ ባለአምስት ኮከብ ሆቴሎችን ማስተዳደር የሚችሉ መሆናቸውም አብራርተዋል።

ለምሳሌ በአንድ ትልቅ ሆቴል ውስጥ ከሚሠሩ ከአምስት መቶ በላይ የአገር ውስጥ ባለሙያዎች የሚያገኙት ደመወዝ ስድስት ወይም ሰባት የሚሆኑ የውጭ ባለሙያዎች ከሚያገኙት ደመወዝ ያነሰ ነው ያሉት አቶ ይታሰብ፤ እነዚህ የውጭ ባለሙያዎች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የተለየ እውቀትና ችሎታ ይዘው ከሆነም የአገር ውስጥ ባለሙያዎችን አሰልጥነው መመለስ አለባቸው ሲሉ አሳስበዋል።



**አቶ ይታሰብ ስዩም**

እንደ አቶ ይታሰብ ገለጻ፤ ዓለም አቀፍ ሆቴሎች በኢትዮጵያ ሥራ ከጀመሩ ከሃያ እስከ ሠላሳ ዓመት ቢሆናቸውም በምክትል ሥራ አስኪያጅ ደረጃ እንኳን የአገር ውስጥ ባለሙያዎችን ማፍራት አልቻሉም። በሆቴሎች ሼፎች፣ የምግብና የመጠጥ ኃላፊዎችን ጨምሮ ሌሎች የየዘርፉ ኃላፊዎች የውጭ አገራት ባለሙያዎች ናቸው።

ከሦስት ዓመታት በፊት ኢንስቲትዩቱ አንድ ጥናት አካሂዶ እንደነበር አስታውሰው፤ በሆቴልና ቱሪዝም ተቋማት የሰለጠነ ባለሙያ ቁጥር ከ26 በመቶ አይበልጥም፤ አብዛኛው ሥራ የሚሠራው በዘርፉ ባልሰለጠኑና በማይመለከታቸው ሰዎች ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የአገልግሎት ጥራት ይሻሻል ከተባለ ዘርፉ በሰለጠኑ ባለሙያዎች ሊመራ ይገባል ሲሉ ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን፤ ለቱሪዝም ዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶት ከተሠራበት ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ትልቅ አስተዋጽዖ ሊኖረው እንደሚችልም ጠቁመዋል።

የአገር ውስጥና የውጭ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ባለሙያዎችን ለማፍራት እየሠሩ ይገኛሉ ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኢንስቲትዩቱ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝና ወደፊትም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

ባለሙያው ስለኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ያለበትን ሁኔታ ሲገልጹ፤ አገሪቷ በቱሪዝም ዘርፍ እምቅ አቅም አላት ያሉ ሲሆን፤ ከዚህ ዘርፍ መጠቀም ባለባት ልክ እንድትጠቀም የባለድርሻ አካላት ቅንጅት ወሳኝ መሆኑንም አስገንዝበዋል።

አገሪቷ ያሏትን እምቅ ሀብቶቿ ለማስተዋወቅና የተሻለ ውጤት እንዲመጣ ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀምና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በቅንጅት እንዲሠሩ ማድረግ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ መሆኑንም አስረድተዋል። አክለውም፣ እስካሁን ባለው ሁኔታ አብዛኞቹ ሥራዎች የሚሠሩት በተናጠል ስለሆነ ገንዘብና ጊዜ እንዲባክን ምክንያት ሆኗል ብለዋል።

# በክልሉ ድርቅና የፀጥታ ችግሮች ባሉባቸው አካባቢዎች የአርሶ አደሩ ምርታማነት እንዳይቀንስ እየተሠራ ነው

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል የድርቅና የፀጥታ ችግሮች በሚስተዋሉባቸው አካባቢዎች የአርሶ አደሩ ምርታማነት እንዳይቀንስ እየተሠራ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። ቢሮው በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች የተከሰተው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች የአርሶ አደሩ ምርታማነት ላይ ተፅዕኖ እንዳያሳድሩ እየሠራሁ ነው ብሏል።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ቢሮው የክረምት ሰብል ልማት ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራው ባለው ሥራ በዚህ የምርት ዘመን በስድስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ሰብል በመዝራት 205 ሚሊዮን ኩንታል እህል ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው።

በዚህ የክረምት ሰብል ልማት መርሃ ግብር የክልሉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ታልሞ እየተተገበረ ሲሆን ለዚህ ይረዳ ዘንድ አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም የሚለማና ይህም ክልሉ ካለው የእርሻ መሬት 75 በመቶ የሚሸፍን መሆኑን ተናግረዋል።

በኩታ ገጠም የሚለማ መሬትን በመለየትና አርሶ አደሩን በኩታ ገጠም የማደራጀት ተግባር እየተሠራ መሆኑን ያስታወቁት አቶ ጌቱ፣ ከዚህ ጎን ለጎን ምርት ማሳደጊያ ግብአቶችን ማሟላት፣ በትራክተር የማረስ ተግባር ማስፋፋት፣ ከስድስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ ኩንታል ማዳበሪያ አቅርቦት እየተከናወነ መሆኑን አንስተዋል።

እቅዱን ለማሳካት ተግዳሮት ይሆናሉ ተብለው የተለዩ በተለይም የድርቁና የፀጥታ ችግሮች ምክንያት ምርት እንዳይቀንስ በልዩ ሁኔታ ተለይተው እየተሠራ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በክልሉ በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች በተለይም በቦረና፣ ሐረርጌ፣ ባሌና ጉጂ አካባቢዎች በተከሰተው የበልግ ዝናብ እጥረት ድርቅ በማጋጠሙ ያልተዘሩ ምርቶች በዚህ የክረምት ወቅት አካባቢዎቹ ምርት እንዲያመርቱ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል።

በድርቁ ወቅት ከፊል አርብቶ አደር ማህበረሰቡ እንስሶቻቸው እንዳይጎዱ በመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶት ድጋፍ ሲደረግ መቆየቱን ምክትል ቢሮ ኃላፊው አውስተው፣ በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ የአካባቢው አርሶ



**አቶ ጌቱ ገመቹ**

አደሮች በተያዘው የክረምት ወቅት የሰብል ልማት ላይ እንዲሳተፉ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት አማካኝነት የማዳበሪያና ምርጥ ዘር አቅርቦት እየተደረገላቸው መሆኑንም ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የፀጥታ ችግር የሚስተዋልባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች መሬታቸው ሳይታረስ እንዳይከርም ከዞንና ወረዳ አደረጃጀቶች ጋር በመሆን በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አቶ ጌቱ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ጌቱ ገለፃ የፀጥታ ችግር በሚስተዋልባቸው አካባቢዎች በተሰጠው ትኩረት ልክ በሌሎች አካባቢዎች እንዲሁ የሚሠራ ቢሆን ከክልሉ አልፎ እንደ አገር የሚገኘው ምርትና ምርታነት ከፍተኛ ነው።

በአካባቢው ለሚገኙ የግብርና ባለሞያዎች ተከታታይ ስልጠና በመስጠት፣ አርሶ አደሩ በቀውስ ወቅት ምርታማነቱን ጠብቆ የሚቆይበት ስልት እንዲሁም ሌሎች ምርት ማሳደጊያ ሥልጠናዎች ሲሰጡ መቆየታቸውን አንስተዋል።

በምዕራብ ኦሮሚያ በተለይም በአራቱ የወለጋ ዞኖች ክልሉ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ግብአቶች በፀጥታ ኃይል በመታጀብ ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ በመደረጉ ምክንያት በዚህ አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች ግብአትን በመጠቀም የግብርና ሥራዎችን እያከናወኑ መሆኑን አረጋግጠዋል።

ሆኖም የፀጥታ ችግሩ ሙሉ በሙሉ ያልተቀረፈ በመሆኑ በማዕከል የሚገኙ የግብርና ባለሞያዎች አርሶ አደሩን በቀጥታ ድጋፍ ሊያደርጉ አለመቻላቸውና አርሶ አደሩ ከዚህ ቀደም የማዳበሪያ ግብአትን ከዩኒየኖችና መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያገኘውን አሁን ራቅ ወዳለ ስፍራ በመሄድ ማግኘቱ ያልተቀረፈ ተግዳሮቶች መሆናቸውን አቶ ጌቱ ተናግረዋል።

ዜና

# «በምክክር መድረኩ የሚሳተፉ ሁሉ እኔ ምን አተርፋለሁ ሳይሆን ኢትዮጵያ ምን ታተርፋለች የሚለውን ይዘው መምጣት አለባቸው»

-ዶክተር ዐቢይ አሕመድ
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በምክክር መድረኩ የሚሳተፉ ሁሉ እኔ ምን አተርፋለሁ ሳይሆን ኢትዮጵያ ምን ታተርፋለች፤ ልጆቻችንስ ምን ያተርፋሉ፤ የሚለውን ይዘው ወደአውዱ መምጣት እንደሚገባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አሳሰቡ። የአገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ አባላት ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጋር ትናንት ውይይት አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ በውይይቱ ላይ እንደገለጹት፤ የአገራዊ ምክክሩ ለልጆቻችን የሚተርፍ ውጤት ያመጣል ተብሎ ይጠበቃል።

በአገራዊ ምክክሩ በአካታችነት እንዲከናወን መንግሥት የበኩሉን ጥረት አድርጓል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የምክክሩ መሳካት በይበልጥ ለቀጣዩ ትውልድ በጎ ነገር የሚያመጣ እንደሚሆን ይታመናል ሲሉ ተናግረዋል።

መንግሥት በኮሚሽኑ ሥራ ጣልቃ የመግባት ምንም ዓይነት ፍላጎት የለውም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ ይልቁንም ለአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ሥራ መሳካት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

በነፃነት እንዲከናወን የሚፈለገው የምክክር መድረኩ እንዲሳካ የኮሚሽኑ አባላት ትልቅ አገራዊ ኃላፊነት እንዳለባቸውም ጠቁመዋል። በዚህ ረገድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኩል ከሕዝብ ተመርጠው የመጡ በመሆናቸው ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ ተብሎ ዕምነት ተጥሎባቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የመጣውን ሁሉ መውቀስ በመለመዱ የወሰንና ማንነት እንዲሁም የዕርቀ-ሰላም ኮሚሽኖች ሥራ አለመሳካቱን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውሰው፤ ኮሚሽኖቹ ያልተሳኩት ሰዎቹ ጥሩ ስላልሆኑ ሳይሆን ተባባሪ ከመሆን ይልቅ የሚጠላለፍና እንቅፋት የሚፈጥር በመብዛቱ ነው ብለዋል። በመሆኑም የምክክር ኮሚሽኑ ሥራ እንዲሳካ ሁሉም ተባባሪ መሆን ይገባዋል ሲሉ አሳስበዋል።

ኮሚሽኑም ከቀድሞዎቹ የእርቀሰላምና የወሰንና ማንነት ኮሚሽኖች ልምድ በመውሰድ ለውጤታማነቱ ይበልጥ ጥረት እንዲያደርግ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ በበኩላቸው፤ የምክክር ኮሚሽኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራውን አጠናቆ የዝግጅት ምዕራፍ ላይ መሆኑን አሳውቀዋል።

አገራዊ ምክክሩ የቅድመ-ዝግጅት፣ የዝግጅት፣ የዋናው ምክክር እንዲሁም የትግበራና ክትትል የሚሉ አራት ምዕራፎች እንዳሉት አስታውሰው፤ በዝግጅት ምዕራፉ ለሥራ የሚያስፈልገውን በጀትና ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት አጠናቆ በቅርቡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለማጸደቅ ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ባለፉት አራት ወራት በርካታ የቅድመ ዝግጅትና የዝግጅት ሥራዎች መከናወናቸውን ጠቁመው፤ የምክክር ሂደት ፍኖተ ካርታን የማዘጋጀት፣ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን እንዲሁም የምክክሩ ውጤቱን ትግበራ የሚከታተሉ ዘርፎች የማቋቋም ሥራ መከናወኑን አስረድተዋል።

ኮሚሽኑ እስካሁን ከ40 የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ውይይት ማድረጉን ገልጸው፤ በተጨማሪ 13 ፓርቲዎች ጋር በተናጠል ስለ ኮሚሽኑ የሥራ ሂደት ውይይት እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ኮሚሽኑ ከአምስት ክልሎችና ከአንድ የከተማ መስተዳድር ካቢኔዎችና ኗሪዎች ጋር ውይይት አድርጓል። በዚህም ፓርቲዎችም ሆኑ የክልል ተወካዮች ከኮሚሽኑ ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ በቀጣይም በክልልና በዞን ደረጃዎች ቢሮ ለመክፈት ውጥን እንዳለው ጠቁመው፤ ቢሮዎቹን ሲከፍት ግን የዩኒቨርሲቲዎችንና የሌሎች ተባባሪ ተቋማትን ቢሮ ሊጠቀም እንደሚችል ጠቁመዋል።

የኮሚሽኑ የዝግጅት ምዕራፍ በጥንቃቄ እየተከናወነ መሆኑን በመግለጽ፤ የዝግጅት ምዕራፉ ሲጠናቀቅ የሚጠበቀው የምክክር መድረክ እንደሚከናወን አስረድተዋል።

በዚህም በ2018 ዓ.ም በማያግባቡን ጉዳዮች ላይ ብሔራዊ መግባባት ላይ ደርሰን ለኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት እንጥላለን ተብሎ ይጠበቃል ሲሉ ፕሮፌሰር መስፍን ተናግረዋል።

# ወጣቶች ለጥፋት ኃይሎች መጠቀሚያ መሣሪያ መሆን እንደሌለባቸው ተገለጸ

አዲስ አበባ፡- ወጣቶች አገራችንን እያለማን አገር ለማፍረስ የሚሹ ኃይሎችን ደግሞ በጋራ በመመከት ለመጪው ትውልድ የበለጸገችና ሰላሟ የተረጋገጠች አገር ማስረከብ ይኖርብናል ሲሉ የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባል እና በፓርቲው የሲቪክና ፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርፍ ኃላፊ ሚኒስትር ዶ/ር ዓለሙ ስሜ ተናገሩ።

ዶ/ር ዓለሙ ስሜ በብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪነት በደብረ ብርሃን እየተካሄደ በሚገኘው አራተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር በማድረግ የችግኝ ተከላውን አስጀምረዋል።

ኃላፊው በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት የተጀመረው አረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ለአገር ግንባታ እና ለቀጣይ ትውልድ መሠረት የሚሆን ሥራ ነው ብለዋል።

የገጠመንን ፈተና እያሸነፍን ብልጽግናችንን እንደምናረጋግጥ ጥርጥር የለውም ያሉት ዶ/ር ዓለሙ፤ ሰላም አልሻም በማለት ገፍቶ የሚመጣ ኃይል ካለ በሚገባው ቋንቋ አስረድተን እንመልሰዋለን ሲሉ ተናግረዋል።

የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ፕሬዚዳንት ወጣት አስፋው ተክሌ በበኩሉ ችግኞችን መትከልና መንከባከብ ለነገዋ ኢትዮጵያ መሠረት የሚጥል በመሆኑ ልዩ ትኩረት እንሰጠዋለን ብሏል።

በአራተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር 6.3 ሚሊዮን ወጣቶችን በማስተባበር ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ችግኞች ይተከላሉ ነው ያለው።

ኢትዮጵያ ብልጽግናዋን ለማረጋገጥ ሌት ተቀን እየሠራች ባለችበት በዚህ ወቅት ጠላቶቿ አገርን ለማፍረስ ቢሠሩም በወጣቶች ጥረት ማንም ኃይል ከብልጽግና ጉዟችን ሊያስቆመን አይችልም ያለው ፕሬዚዳንቱ በጠቅላይ ሚኒስትራችን የተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ስኬታማነት ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት የላቀ ሚና አለውም ማለታቸውን ፓርቲው በማህበራዊ ገጹላይ አስታውቋል።

# «በኢትዮጵያ ለሚታየው የሰላም መደፍረስ ዋነኛው መንስኤ ወያኔ ነው»

-ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
የኢፌዴሪ ፖሊሲ ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

**ፍቃዱ ከተማ**

አርባ ምንጭ፡- በለውጡ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚታዩ የሰላም መደፍረሶችና አሁን ለሚታዩ ችግሮች ዋነኛው ምክንያት አምባገነናዊ የሆነውንና እኔ ያልኩት ካልሆነ ወይም እኔ አገር ካልገዛሁ ኢትዮጵያ መፍረስ አለባት ብሎ እየሠራ ያለው ወያኔ ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ፖሊሲ ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ገለጹ።

ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አርባምንጭ ከተማ ላይ «ሰላም ዴሞክራሲና እውነተኛ ፌዴራሊዝም» በሚል ርዕሰ ጉዳይ ባዘጋጀው «ስለኢትዮጵያ» የተሰኘ መድረክ ላይ እንደገለጹት፤ በትጥቅ ትግል ወደ ሥልጣን የመጣው ወያኔ ከፍጥረቱ አንስቶ በሴራ ሕዝቦችን በመከፋፈል፣ የተለየ ሃሳብ ያላቸውን በማሳደድና በመግደል እውነተኛ ባህሪው የተገለጠ ነውረኛ ድርጅት ነው።

ፕሮፌሰር በየነ አክለውም ሕወሓት የተባለው አሸባሪ ቡድን ተፈጥሮው አምባገነናዊ፤ ሁሉንም ነገር በመሣሪያ ብቻ ለመፍታት የሚሞክር የአመጽና የችግር ቡድን ነው ብለዋል። አሁን በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በተለያየ ስያሜ የሽብርና የጭፍጨፋ ተግባር ከሚፈጽሙ ኃይሎች ጀርባ ያለው የሽብር ቡድን ኢትዮጵያ ጠል የሆነው ወያኔ ነው ሲሉ አጽንኦት ሠጥተው ገልጸዋል።

ወያኔ በአገር ውስጥ ከሚፈጥረው የሰላም መደፍረስና አገር ማፍረስ ሥራ ጎን ለጎን የኢትዮጵያ ገናናነትና ታሪካዊነትን የሚጠሉና የሚፈሩ የውጭ ኃይሎች ሴራም አለበት ያሉት ፕሮፌሰር በየነ፤ እነዚህን ተረድቶ ሴራቸውን ለማክሸፍ ኢትዮጵያውያን በጠላት ወሬ ሳይከፋፈሉ በአንድነት ሊቆሙ ይገባል ሲሉ ምክር ለግሰዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተፈጥሮው አንዱ በሌላው ላይ ተነስቶ ያጠቃበት ሁኔታ አልነበረም፤ አሁንም የለም ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ከእያንዳንዱ ግጭት ጀርባ ሆኖ የግጭት አጀንዳ የሚፈጥረውና ቤንዚን እየጨመረ እሳት የሚያቀጣጥለው የጥፋት ኃይል የሆነው አሸባሪው ሕወሓት ነው ሲሉ አጽንኦት ሰጥተው ገልጸዋል። የዚህ ዋነኛ ምክንያት ደግሞ አሸባሪው ቡድን ህልውናዬ የሚጠበቀው በሕዝቦች ግጭትና ፍጅት ብቻ ነው ብሎ ስለሚያምንና ለዚህም ስለሚሠራ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት «ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች» በሚል ርዕስ በ12 ከተሞች ላይ ለማከናወን አቅዶ እያካሄደ ያለው ስለኢትዮጵያ የአውደርዕይና የፓናል ውይይት መድረክ ከዚህ ቀደም በጂግጂጋ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረርና ሃዋሳ በተለያዩ ታላላቅ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የተካሄደ ሲሆን የአርባምንጩ መድረክ አምስተኛው ነው።

# «ሕወሓት በጦርነቱ ...

ከገፅ 1 የዞረ

በአገር ደረጃ በጦርነቱ ምክንያት የተፈጠረው ቀውስ ከፍተኛ ቢሆንም በትግራይ ሕዝብ ላይ የደረሰው ግን እጅግ አስከፊ ነው ያለው ሻለቃ አትሌት ኃይሌ፤ ከጦርነት ጥፋት እንጂ አንዳችም መልካም ነገር ስለማይገኝ ለሁሉም የሚበጀው አሁን የተጀመረውን የሰላም ጥረት በአግባቡ መጠቀም ብቻ ነው ብሏል።

ከጦርነቱ በፊት ከአገር ሽማግሌዎችና ከሃይማኖት አባቶች ጋር በመሆን ወደ መቀሌ በመሄድ ከዶክተር ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል ጋር አለመግባባቶቹ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ በተደጋጋሚ ብዙ ጥረት ማድረጋቸውን ያነሳው ሻለቃ ኃይሌ፣ ዳሩ ግን በሕወሓት በኩል ቁርጠኝነት ባለመኖሩ ጥረቱ ፍሬያማ ሳይሆን ቀርቶ የብዙዎችን ሕይወት ያረገፈና የዘመናት ጥረት ውጤቶች የሆኑትን የአገሪቱ ሀብቶች ወደ ዶግ አመድ የቀየረው ጦርነት መከሰቱ በቁጭት ገልጿል።

በወቅቱ የሕወሓት ባለሥልጣናት ትግራይን እንደ አንድ የኢትዮጵያ ክልል ሳይሆን እንደ አንድ አገር አድርገው ከማቅረባቸው በተጨማሪ ለውይይት የሚያቀርቡት ነጥቦች እንደ የአንድ የክልል ባለሥልጣናት የሥልጣን ገደብ ባለመሆኑ ድርድሩ እንዲመክን ትልቅ እንቅፋት እንደነበር የጠቆመው ሻለቃ ኃይሌ፣ አሁንም «ቀይ መስመር፣ ሰጥቶ መቀበል» የሚሉ የቅድመ ድርድር ቃላቶች የድርድሩ ሂደት እንዳያደናቅፉ ያለውን ስጋት ገልጿል።

እንደ ሻለቃ ኃይሌ ማብራሪያ፣ የሰላም ውይይት ክርክር ስላልሆነ ቀይ መስመር የሚባል ነገር ባይነሳ ጥሩ ነው። አገር ማዳን ከተፈለገ ሁሉም ወገን ሰጥቶ ለመቀበል ብቻ ሳይሆን የመተውም ኃላፊነት አለበት። ያም ሆኖ ሕወሓት እንደ ከዚህ በፊቱ «እኩል ነን፣ ትግራይ አገር ናት ወዘተ» የሚሉ አፍራሽ ነጥቦችን ይዞ ለሰላም ውይይት ባይቀርብ ጥሩ ነው ብሏል።

በጦርነት ያለቁ በርካታ ዜጎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ወደሰላማዊ ውይይት ከመግባት የበለጠ ነገር የለም። በኢትዮጵያ መንግሥትም በኩል ቢሆን አሁን ያሉ የኑሮ ውድነትና የሰላም እጦት ችግርና የውጭ አገሮች ጣልቃ ገብነት ግርግር በቂ በመሆናቸው ለሰላም ያለው ቁርጠኝነት ላይ መጽናት ይጠበቅበታል።

ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ ሕወሓት ለፌዴራሉ መንግሥት አንገዛም በማለት ሕዝቡን ለሌላ ችግር ማጋለጡ ተገቢ ባለመሆኑ ለሰላማዊ ውይይቱ ዝግጁ እንዲሆንም በአጽንኦት አሳስቧል።

መጀመሪያውኑ የትግራይ ሕዝብ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ዋዝቦች በክልሉ ታጥሮ የሚኖር ሕዝብ ሳይሆን በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚኖርና በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደር ሕዝብ መሆኑን የመሰከረው ሻለቃ አትሌት ኃይሌ፣ ድርድሩም ቢሆን የሚካሄደው በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል እንጂ ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ሌላው አካል ከትግራይ ሕዝብ ጋር ጸብ እንደሌለው ሊታወቅ ይገባል ብሏል።

ኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጠላቶች ኢላማ በመሆን ሕዝቡ በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ተጋላጭ በሆነበት ጊዜ ውስጥ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የጦርነት ወሬ እንዳይሰማ አደራዳሪ አካላት፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያ ወዳጆች የሰላም ውይይቱ ውጤታማ እንዲሆን የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡም ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ጠይቋል።

# በክልሉ የመልካም..

ከገፅ 1 የዞረ

ዘንድ ተመራጭ ክልል እየሆነ መምጣቱንም ጠቁመዋል።

የክልላዊ መንግሥት መመሥረት ዕውን ከሆነ በኋላም ባለፉት ሁለት ዓመታት የሕዝቡን ፍላጎት በመለየት በተለይም በመንገድ፣ ውሃ፣ መብራት እንዲሁም ሌሎች መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት ቅድሚያ ተሰጥቶ መሠራቱንም አስታውሰዋል።

ይሁን እንጂ ለሕዝቡ ፍላጎትና ጥያቄ በአንድ ጀምበር ምላሽ መስጠት አይቻልም ያሉት አቶ ደስታ፤ በቀጣይ ትግላችን የሚሆነው ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ ሥራ አጥነትና ድህነት በመቅረፍ እንዲሁም ብልሹ አሠራሮችን መታገልና የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል ነው ብለዋል።

የሲዳማ ሕዝብ ባህላዊ የእርቅና የግጭት አፈታት የአፊኒ ሥርዓትን በመጠቀም በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች ሠላምና ጸጥታ በመስፈኑ በቀጣይም ይህንን ዕሴትና ልማት አጠናክሮ ማስቀጠል የሁሉም ድርሻ እንደሚሆንም አስገንዝበዋል።

የክልሉን ሕዝብ ኑሮ በማሻሻል ወደ ለውጥ ጎዳና የማምራት ዕድሉ በእጃችን በመሆኑ ያለንን ሀብት በአግባቡ ተጠቅመን ለመልማት ጊዜው አሁን ነው ብለዋል።

በክልሉ ለሥራ አጥ ዜጎች በተፈለገው መጠን የሥራ ዕድል ለመፍጠር አለመቻሉን እንደ ተግዳሮት ያነሱት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ዜጎች ሥራ ወዳድና ፈጥረው መሥራት የሚችሉበትን የአመለካከት ለውጥ እስከሚያመጡ የክልሉ መንግሥት የሚጠበቅበትን ሁሉ እንደሚያደርግም አመልክተዋል።

በክልሉ ባለፉት ሁለት ዓመታት በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች የተከናወኑ አበረታችና ተስፋ ሰጪ ተግባራትን አጠናክሮ ለማስቀጠልና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሕዝቡ ፍላጎትና ጥያቄ ምላሽ በመስጠት የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች የማይነሱበት ክልል ለማድረግ በየደረጃው ከሕዝቡ ጋር በመቀናጀት ይሠራልም ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላም፤ ሰላም፤ ሰላም!

ኢትዮጵያ የሀገር ውስጥና የውጭ ጠላቶቿ ሰላሟን ለማደፍረስ በሚያደርጉት ርብርብ ተደናግጣ ለአጸፋዊ ምላሽ ተቻኩላ አታውቅም:: ጦርነት የልጆቿን ውድ ህይወት እንደሚቀማ፣ ሀብትና ንብረት እንደሚያወድም ትገነዘባለች:: ለሰላም አይነተኛው መፍትሄ ጦርነት አለመሆኑን በመረዳትም ሰላማዊ አማራጭ ላይ አተኩራ የምትሰራውም ለዚሁ ነው::

አሸባሪው ሕወሓት ከሀገራዊ ለውጡ ማግስት አንስቶ ኢትዮጵያን ለመበትን ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ተላላኪዎቹን መጠቀም ነው:: በመላ ሀገሪቱ የሞት ድግስ ነጋ ጠባ ሲያወጣ፣ የትግራይን ህዝብ አግቶ ሲያሰቃይ ከድርጊቱ እንዲታቀብ ለማድረግ መንግስት ሰላማዊ አማራጮችን እንጂ ጦርነትን አልተጠቀመም:: ከዚህ ጦርነት በፊት መንግስት በርካታ ሰላማዊ አማራጮችን ተጠቅሟል:: የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች ፣ እናቶች ፣ዲፕሎማቶች መቀሌ ተመላልሰው ስለ ሰላም ብዙ ደክመዋል:: መንግስት በተገኙ አጋጣሚዎች ሁሉ ሰላማዊ መፍትሄን እንደሚከተል ሲያሳውቅም ቆይቷል፤

በሰሜን እዝ ላይ ክህደት እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ የሰላም አማራጭን ተከትሎ ነው የቆየው:: የቡድኑ ክህደት ግን ነገሮችን ቀየራቸውና ጦርነት የግድ ሆነ:: በዚህ የሕግ ማስከበር ስራ ግን አሸናፊው ጦርነት የጫረው አሸባሪው ሕወሓት ሳይሆን ለሰላም ሰላማዊ መፍትሄ ላይ አበክሮ የሰራው የኢትዮጵያ መንግስት ሆነ:: በእዚህ ጦርነት ትህነግ ጥቂት የማይባሉ መሪዎቹንና አያሌ የትግራይ ልጆችን ገብሮ ወደ ተፈጠረበት ዋሻ ተመለሰ:: ሰላማዊ መፍትሄውን የገፋውና ጦርነትን አማራጭ ያደረገው ትህነግ በመረጠው መሳሪያ ተዋግቶ ተሸነፈ:: የሰላም አማራጭን የተከተለው መንግስት ተገዶ በገባበት ጦርነት ድል አደረገ::

ከስህተቱ የማይማረው ይህ ቡድን መንግስት የተናጠል የተኩስ አቁም በማድረግ ወታደሮቹን ከትግራይ ክልል ሲያስወጣ የጦርነት አባዜው አገረሸበት:: የአማራና አፋር ክልሎችን የተለያዩ ዞኖች በመውረር ታሪክ ይቅር የማይለው ጥፋት ፈጸመ:: በርካታ ንጹኃን ዜጎችን በግፍ ጨፈጨፈ፤ ህጻናትና ባልቴቶችን ጨምሮ በርካታ ሴቶች በታጣቂዎቹ ተደፈሩ፤ ሚሊዮኖች ተፈናቀሉ፤ በዚህም ሳያበቃ ራሱ ከፈጠራቸው ተላላኪዎችና ከውጪ የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር በመሆን የመንግስትነት ስልጣን በኃይል ለመቆጣጠር ሰሜን ሸዋ ድረስ በመዝለቅ ብዙ ርቀት ተጓዘ::

ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ የሀገር ውስጥና የውጭ ተባባሪ ሀይሎቹ አዲስ አበባ ተከባለች፤ ነገሩ አብቅቷል፤ የውጭ ዜጎች ኢትዮጵያን ለቃችሁ ውጡ ሲሉ ይጮሁ ጀመር፤ መጮህ ብቻም ሳይሆን አንዳንድ ምዕራባውያን ወደ ጎረቤት ሀገሮች መሄድ ያዙ፤ የጎረቤት ሱዳን መንግስት እንኳ ዜጎቿ ኢትዮጵያን ለቀው እንዲወጡ አሳሰበ፤ እነዚህ ኃይሎች ቡድኑ የሚያወርደውን የሽብር ዘፈን በጭብጨባና በሆይሆይታ አደመቁለት::

ጦርነቱ ግን በመንግስት ኃይሎች ተጋድሎ በድል ተጠናቀቀ:: ሰላም ለማምጣት ሰላማዊ አማራጭን የሚከተለው የኢትዮጵያ መንግስት ተገዶ በገባበት ጦርነት ድል አድርጎ ሀገርን ከከሀዲው ትህነግ፣ ተላላኪዎቹ እና ተባባሪዎቹ ምእራባውያን ታደገ:: ትህነግን ለሁለተኛ ጊዜ በማሸነፍ ኢትዮጵያና ህዝቧ ላይ ተደቅኖ የነበረውን የስጋት ደመና ብን ብሎ እንዲጠፋ አድርጎታል::

ይህም የጦርነት ዘመቻ በአሳፋሪ መልኩ አያሌ የትግራይ ህዝብ ልጆችን ገብሮበት በዜሮ ተባዛ:: በጀመረው ጦርነት ራሱ ተሸነፈ:: የሀገር ሀብት ወደመ፤ የሀገር ገጽታ ተበላሸ:: ጦርነቱን በመቀልበስ ሂደት ጀግኖች ኢትዮጵያውያንም ተሰዉ:: ሀገሪቱ ለተለያዩ የምእራባውያን ጫናዎች የተዳረገችውም ይህንኑ የትህነግን እና የተባባሪዎቹ ምእራባውያንን የጦርነት አባዜ ተከትሎ ነው::

ለኪሳራ ከዳረጉት ከትኩሶቹ የጦርነት ታሪኮቹ የማይማረው ከንቱ ቡድን ዘንድሮም ለሦስተኛው ጦርነት እየተዘጋጀ ነው:: ክረምትን ተገን በማድረግ ጦርነት ለመክፈት እየተዘጋጀ ከመሆኑ በተጨማሪ ተባባሪዎቹ የውጪ ኃይሎችና የሀገር ውስጥ ተላላኪዎቹ በኢትዮጵያ ላይ የተቀናጀ የጥፋትና የጥቃት ዘመቻዎቻቸውን ከፍተዋል:: የተለመደውን የተቀናጀ ዘመቻ መፈጸማቸውን ቀጥለዋል::

የሱዳን መንግስት የኢትዮጵያን መሬት በኃይል መያዙ እንዲሁም በሀገሩ ለሚገኙ የትህነግ ታጣቂዎች የሚሰጠው ድጋፍ አንሶት አሁንም ከትንኮሳ ያልተናነሱ ተግባሮች እየፈጸመ ይገኛል:: አሸባሪው ሸኔ በጦርነት ቢሸነፍም በንጹኃን ዜጎች ላይ አሰቃቂ ጥቃት በመፈጸም ከትህነግ የተሰጠውን የቤት ስራ መወጣቱን ቀጥሏል::

ይህ ሁሉ ባለበት መንግስት አሁንም በሀገሪቱ ሰላምን ለማረጋገጥ ሰላማዊ መፍትሄን ዋና አማራጩ አድርጎ ይዞ እየሰራ ነው:: የተለያዩ ወገኖች መንግስትና ቡድኑ እንዲወያዩ ሙከራዎችን ሲያደርጉ መንግስት ሁኔታውን በአዎንታዊነት ተቀብሎ እየተንቀሳቀሰ ነው:: ተደራዳሪ ወገን በመሰየምም ለሰላም ንግግሩ ዝግጁ መሆኑን አረጋግጧል:: ዜጎች፣ የፖለቲካ ቡድኖችና ሌሎችም ኃይሎች በሀገራቸው ለዘላቂ ሰላም እንዲተጉ ለማድረግ እየተሰራ ነው:: በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት ላይ መድረስ እንዲቻል ለማድረግም ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ስራ ገብቷል::

መንግስት እስከ አሁን ወደ ጦርነት የገባው ተገዶ ነው እንጂ በወሳኝነት ሰላማዊ መንገድን ነው ምርጫው አድርጎ እየሰራ ያለው:: ቀደም ሲል ሰላማዊ መንገድን መምረጡ በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ የተለሳለሰ ቢያስመስለውም ሰላማዊ አማራጭ ትልቁ መሳሪያ መሆኑን በማመን ሰርቷል፤ አሁንም ይህንኑ እያረጋገጠ ነው::

የኢፌዴሪ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ ሰሞኑን እንደገለጹት ፤ መንግስት ለሰላም ቅድሚያ መስጠቱን ቀጥሏል:: በሩን ለሰላም ሲከፍት ከእነሙሉ ዝግጁነቱ፣ አቅሙና ብቃቱ ነው::

የሽብር ቡድኑ ሰላማዊ አማራጭን እንደ ማዘናጊያ ሲጠቀምበት ቆይቷል፤ መንግስት ይህን አይነቱን መንገድ አይከተልም:: የሰላማዊ መንገድ ፍሬው ብዙ መሆኑን ይረዳል:: ጦርነት የዜጎችን ሕይወት እንደሚቀጥፍ፣ እንደሚያፈናቅል፣ ሀብትና ንብረትን እንደሚያወድም ያውቃልና አሁንም ይህን አማራጭ በፍጹም አይከተልም:: አሸባሪውም ኃይል ለዳግም ጦርነት ከመዘጋጀት ወጥቶ የሰላም እድሉን መጠቀም መቻል ቢችል ትርፉ ብዙ ይሆናል።

የጦርነት ጉሰማዎች አያዋጡም፤ ባለፉት ጦርነቶች የጠፋውን ህይወት የወደመውን ሀብትና ንብረት የተበላሸውን የሀገር ገጽታ መለስ ብሎ መቃኘት የሰላማዊ አማራጭን ፋይዳ ከፍተኛ ያደርገዋል:: በጦርነት ፍላጎትን ማሳካት እንደማይቻል የመንግስት ጽኑ እምነት ነው:: የተረጋጋ የፖለቲካ ስርአትን ለመፍጠር መንግስት ለሰላም ሙሉ ለሙሉ ዝግጁ መሆኑን አረጋግጦ እየሰራ ነው:: አሁንም ሰላማዊ አማራጭን ለሰላም ማዋል ይገባል!!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ለዘላቂ ሰላም ፊታችንን ወደ ምስራቅ በማዞር ተገቢውን ተሞክሮ እንቅሰም

**ዳንኤል ዘነበ**

የጋዜጠኛ ዘላለም መሉ የመጀመሪያ ስራ የሆነውን "ብር አዳዩ መሪ" መጽሐፍን በድጋሚ እያነበብኩ ነበር። መጽሐፉን አንብቤ ስጨርስ አዕምሮዬ አንድ ሃሳብ ማውጣት ማውረድ ጀመረ። ሐምሌ 27 ቀን 2010ዓ.ም ጂግጂጋ ከተማ ላይ የነበረውን ጭንቅ ተመልሼ እንዳስብ አድርጎኛል። የክልሉ አመራሮች አቅደው 'ሄጎ' የተባለ ገዳይ ቡድን አደራጅተው ሃይማኖትና ብሔራቸው ተለይቶ የተጨፈጨፉት ንጹሃን ሁናቴን አስታወሰኝ።

በወቅቱ በሶማሌ ክልል ዋና ከተማ ጂግጂጋን ጨምሮ በክልሉ የተለያዩ ከተሞች የነበረው እንቅስቃሴ ክልሉ ዳግም ወደ ሰላም ይመለሳል ለማለት የሚያስደፍር አልነበረም። ነገር ግን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ በወሰደው አፋጣኝ እርምጃ ትኩሳቱ ሊበርድ ችሏል። አቶ ሙስጠፌ ሙሐመድ ወደ ስልጣን ሲመጡ ደግሞ ነገሮች ሙሉ መልካቸውን ቀይረዋል።

ነሐሴ 2010 ዓ.ም ሶማሌ ክልልን ለበርካታ ዓመታት በርዕሰ መስተዳድርነት ሲመሩ የነበሩትን አብዲ ሙሐመድ ኡመርን የተኩት አቶ ሙስጠፌ ሙሐመድ፤ ጂግጂጋ ዳግም የሰላም አየር ይነፍስባት ይሆን? የተባለላትን ከተማ ታሪክ ቀየሩ። በአጭር ጊዜ ክልሉ ከስጋት ቀታናነት ወደ ሰላም እንዲሸጋገር አደረጉ።

ለዚህ ደግሞ የክልሉ መንግስት ከምንም በፊት ሰላም ይቅደም በሚል ተጨባጭ ሥራዎችን ማከናወን ችለዋል። ለሰላም ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ህዝብም በተግባር ተክሷል። በአሁኑ ወቅት በሱማሌ ክልል ዜጎች በሃይማኖታቸውም ሆነ በብሄራቸው ሳይሸማቀቁ በነጻነት የእለት ተለት እንቅስቃሴያቸውን ከመተግበርም በላይ በነጻነት ሃሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ ተደርጓል። በውጤት ደረጃ ሲለካም ተጨባጭ ለውጥ ተገኝቷል።

እዚህ ጋር የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንትና አስተዳደራቸው በክልሉ አስተማማኝ ሰላም በማስፈን የሰሩት አኩሪ ሥራን የመንግስት ቀዳሚ ተግባራት ምን መሆን ይገባቸዋል ሲሉ በዘርፉ የተሰማሩ ምሁራን፣ የፖለቲካ ሳይንስና የህግ ሊቃውንት ከሚያቀርቧቸው ሃሳቦች ጋር የሚጣጣም ነው። ከዚህ ውስጥ ቶማስ ሆብስ የተባለው ሊቅ ሌዋታን (Leviathan) በሚል ርእስ ባሰናዳው የፖለቲካ ፍልስፍና ጽሑፉ፤ "ያለ መንግስት - የማያቋርጥ ሰላም፣ ያለ መንግስት - ህግ እና ስርዓትን ማስጠበቅ፣ ያለ መንግስት - ዜጎችን ከእርስ በርስ እና ከውጭ ጠላቶች መጠበቅ" እንደማይቻል ያስቀምጣል።

ክሌር አንደርሰን የተባለ ሌላ ጸሐፊ ደግሞ "ማንኛውም መንግስት የህዝቡን ደህንነት መጠበቅ፣ መሰረተ ልማት መዘርጋት እና የህዝቡን ገጽታ በመገንባት ዙሪያ ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ይጠበቅበታል" ሲል የቶማስን ሃሳብ ያጠናክራል። በዚህ ጸሐፊ እይታ የአንድ መንግስት ዋነኝ ኃላፊነት የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ከጥቃት መጠበቅ መሆኑን አጽንዖት ሰጥቶ ይናገራል።

ከሊቃውንቱ እሳቤ የህዝብን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ የመንግስት ቀዳሚ ተግባር እንደሆነ ከተገነዘብን፤ የሶማሌ ክልልን ከስጋት ቀጣናነት ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ያሻገሩትን ሰው አለማድነቅ እንዴት ይቻላል?!

በሶማሌ ክልል ውስጥ የሚፈጠረው ሰላምና መረጋጋት እንደ ሀገር ካለው ጥቅም ባለፈ ለቀጣናው መሰረታዊ መፍትሄን በማምጣት የአፍሪካ ቀንድ አገራትም እንዲቀራረቡና እንዲረጋጉ የሚያደርግ ጭምር መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ደረጃ ወሳኝ የሆነውን ክልል ከስጋት ወደ ሰላም ቀጣና ለመቀየር እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታዎች የነበሩ ቢሆንም፤ በክልሉ ጠንካራ የመንግስት መዋቅር በመዘርጋት አስተማማኝ ሰላም ለማስፈን ተችሏል። ይህም ክልሉን ሁሉም ዜጎች በአንድ መነጽር የሚታይበት አድርጎታል።

በሶማሌ ክልል ከለውጡ በኋላ አስተማማኝ ሰላም በመፍጠር የተገኘውን ድል በሁሉም ክልሎች ቢደገም ስል አስባለሁ። በእርግጥ በፌዴራልም ሆነ በክልል መንግስቶች በሀገሪቱ አስተማማኝ ሰላምን ለማስፈን ጥረቶች እየተደረጉ እንደሚገኝ አይካድም። ይሄንን ጽሑፍ እያዘጋጀሁ ባለሁበት ቅጽበት እራሱ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፤ በኦሮሚያ ክልል በንጹሃን ላይ ጭፍጨፋ የፈጸሙ የሽብር ቡድኖች ላይ የተቀናጀ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን እያብራሩ ነበር።

የመንግስት ጥረትና ድካም የማይካድ ቢሆንም፤ የክልል መስተዳድሮች ከሶማሌ ክልል መንግስት እና ከክልሉ ፕሬዚዳንት ብዙ ሊማሩ ይገባል። ክልሎች ወደ ምስራቅ መመልከት ልምድ መቅሰም እንደሚጠበቅባታ አስባለሁ፤ አምናለሁም። በቀናነት በመማማር ፈተና የሆኑብንን ችግሮች በመፍታት ወደ አሰብንበት መድረስ እንችላለን።

በቤኒሻንጉል፣ በአማራ ሆነ በሌሎች ክልሎች ዜጎች ከስጋት በጸዳ መልኩ መንቀሳቀስ የሚያስችላቸውን ሁኔታ ለመፍጠር ከሶማሌ ክልል ተሞክሮ ብዙ መማር እንደሚችል እገምታለሁ። በእርግጥም በእነዚህ ክልሎች የሚወሰዱ የህግ ማስከበር ስራዎች በዘላቂነት የመፍትሄ ምንጭ እንዲሆን የተቀናጀ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው።

በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በንጹሃን ዜጎች ላይ በአሸባሪዎች ጥምረት እየተፈጸሙ የሚገኙ አሰቃቂ የሰላማዊ ሰዎች ግድያዎች በቀጣይ ሊደገሙ አይገባም። በተለይ ኦሮሚያ፣ አማራና ቤኒሻንጉል ክልሎች ህግና ሥርዓትን በማስከበር የዜጎች በሰላም የመኖር ተቀዳሚውን የመንግስትነት ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል። አሁን በክልሎቹ ዘላቂ የተረጋጋ የፖለቲካ ስርአት መፍጠር ውዴታ ሳይሆን ግዴታ እንደሆነ አምኖ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ የግድ ይላል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 13ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የተናገሩት አንድ ንግግር ነበር። "የአማራ ክልል እናቶች ማታ ማታ በሚሰማው የጥይት ድምጽ መተኛት አይችሉም ነበር። በክልሉ በተወሰደው የህግ ማስከበር ስራዎች የአማራ እናቶች የጥይት ድምጽ እንዳይሰሙ አድርጓል"። ይህ አይነቱ ውጤት በኦሮሚያ ክልል እንዲመጣ እሻለሁ።

የኦሮሞ እናቶች የጥይት ድምጽ እንዳይሰሙ ማድረግ ያስፈልጋል። ባለፉት አራት ዓመታት በወለጋ የሚገኙ እናቶች እንባን ሰላምን በማስፈን ማበስ፤ በቤኒሻንጉል በግፍ የሚፈሰውን የዜጎችን ደም ማስቆም ያስፈልጋል። መንግስት የግድ ይህን ማድረግ ያለበት በሁለት ምክንያቶች ነው።

የመጀመሪያው መንግስት ህግና ሥርዓትን የማስከበር ሥራው ወቅታዊ ጉዳይ ሳይሆን የሁልጊዜ ሥራው በመሆኑ ነው፤ በሁለተኛው ደግሞ በክልሎች ሰላምን በማስፈን የህግ የበላይነት ማስከበር አለመቻል በህዝቦች መካከል እርስበርስ መከፋፈል ከዛም አልፎ ግጭት ሊፈጥር ስለሚችል ነው። ይህ ደግሞ በዙሪያችን ለከበቡን ጠላቶቻችን "ሠርግና ምላሽ" እንደሚሆን ይታመናል።

አሁን አሁን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ መንግስት በተለያዩ አካባቢዎች በሽብር ቡድኖች የሚፈጸሙ ግድያዎች፣ ማፈናቀሎች፣ ዝርፊያዎች ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር ባለመቻሉ እንደ አቅመ ቢስ እያስቆጠረው ይገኛል። አስተሳሰቡ በራሱ የተሳሳተ ቢሆንም መንግስት ግን አስተሳሰቡ የተጨማሪ ችግር ምንጭ ሳይሆን በተግባር ሊያርመው ይገባል።

የክልል መንግስታትም እንደ መንግስት ካለባቸው ህገመንግስታዊ ኃላፊነት አንጻር የየክልሎቻቸውን ሰላምና ጸጥታ በማስጠበቅ ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ደግሞ ፊታቸውን ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ በማዞር ተገቢውን ተሞክሮ መቅሰም ይጠበቅባቸዋል እላለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የሴቶች ጉዳይ- የሁሉም ጉዳይ

**በአክበረት ታደሰ**

ይህንን ጉዳይ ለማንሳት ያስገደደኝን አጋጣሚ ላስቀድም። ሴት እንደመሆኔ መጠን ወርሐዊ ግዴታዬ ላይ ነበርኩኝና የሴት ንጽሕና መጠበቂያ አዘውትሬ ወደ ምገዛበት ሱቅ ሄድኩኝ ። ኢቭ ሞዴስ ስጠኝ ብዬ መቶ ብር ሰጠሁት እሱም የንጽሕና መጠበቂያውንና መልስ ደግሞ ሰላሳ ብር ሰጠኝ። የእውነት ደነገጥኩ ምክንያቱም ከአንድ ወር በፊት አርባ ብር የገዛሁት ሞዴስ ነው አሁን ሰባ ብር የገባው። ጭማሪው በጣም የተጋነነ ነው። እየተነጫነጭኩም ቢሆን ገዝቼ ተመለስኩ።

በዛ ቅጽበት ግን ወደ ሀሳቤ የመጣው ይህንን ዋጋ መክፈል የማይችሉ ሴቶች አማራጭ ምን ሊሆን ነው የሚለው ነው። ኮንዶም በሽታ ለመከላከል፣ እንዲሁም ያልተፈለገ እርግዝና ለማስወገድ በሚል መንግሥት በነጻ ኅብረተሰቡ እንዲጠቀም አመቻችቷል። በነጻ( ያለ ክፍያ) እየተሰጠው ደግሞ የማይጠቀመው ብዙ ነው ለዚህም ማሳያ የሚሆነው አሁን ላይ ቁጥሩ እየጨመረ ያለው የኤች አይ ቪ እና የአባላዘር በሽታዎች ስርጭት እንዲሁም፣ እርግዝናን የሚያስወርዱ ሴቶች ብሎም ተማሪዎች ቁጥር ነው። የወር አበባ (menstruation) አንዲት ሴት ፈለገችም አልፈለገችም የተፈጥሮ ግዴታዋ በመሆኑ፣ እስከተወሰነ እድሜ ድረስ በየወሩ የምታየው ተፈጥሯዊ ነገር ነው።

ይህን ለመቋቋም ደግሞ የንጽሕና መጠበቂያ ሞዴስ ያስፈልጋታል። ወደ ገጠሩ የሀገራችን ክፍል ይህን የንጽሕና መጠበቂያ ሞዴስ የማግኘት እድል ስለሌላቸው ( ማግኘት ባለመቻላቸው)፣ በኩበት፣ በጨርቅ፣ በቃጫ፣ በፍራሽ ስፖንጅ ( እሱም ከተገኘ ነው) ብቻ ደሙን ለተወሰነ ሰዓት ሊይዝላቸው በሚችል ነገር ሁሉ ለመቋቋም ይሞክራሉ። በዚህ የተነሳ በየወሩ ሴት መሆናቸውን ያማርራሉ ተፈጥሮን ይጠሏታል። በዚህ ጊዜያቸው ላይ ከሰው ይገለላሉ። ወደትምህርት ገበታቸውም አይሄዱም። ቀናቸውን እስኪጨርሱ፣ ለብቻቸው በስቃይ ውስጥ ነው የሚያሳልፉት።

10 ፍሬ የሚይዘው የንጽህና መጠበቂያ ሞዴስ፣ ከስምንት ብር ተነስቶ አሁን ሰባ ብር እየተሸጠ ነው። ጥቂት የወር ገቢ ያለን ሴቶች ቢወደድብንም እየተነጫነጭንም ቢሆን እንገዛለን። የኑሮ ውድነቱ እዚህ ደረጃ ላይ በደረሰበት በአሁኑ ወቅት፣ የቤት ውስጥ ብዙ ኃላፊነት ያለባቸው ሴቶችስ ይህን የመግዛት አቅም ይኖራቸዋል? በከተማ ያሉ የመግዛት አቅም የሌላቸው ሴቶችስ ምን ያደርጋሉ?። ይገዛሉ ወይስ ይተዉታል? ሲተዉትስ ምን አይነት አማራጭ ነው የሚጠቀሙት? የሚለው አሳሳቢ ጉዳይ መሆን አለበት።

በሚጠቀሟቸው አማራጮች ምክንያት ስንቶች ለማህጸን ኢንፌክሽን እና ተያያዥ የማህጸን ሕመሞች እንደተጋለጡ ቤት ይቁጠረው። ሴት ልጅ እናት ናት፣ እህት ናት፣ ሚስት ናት፣ ደግሞም ሴት በሀገር ትመሰላለች። እንደሚታወቀው በሀገራችን ደግሞ ሴት ብዙ ኃላፊነት አለባት ። የቤተሰብ ኃላፊነት ጫናው የሚወድቀው ሴቷ ላይ ነው። በተለይ ደግሞ የቤት እመቤት የሆኑ እናቶች ላይ ጫናው የበረታ ይሆናል። አሁን በሀገራችን ላይ ባለው የኑሮ ውድነት፣ አባወራ ሰርቶ ገንዘብ ቢያመጣም ሴት ግን ገንዘቡን አብቃቅታ ቤተሰቧን መመገብ ማስተዳደር ይጠበቅባታል።

ሴት ልጅ ተፈጥሮ ብቻዋን እንኳን የምታሸክማት ብዙ ኃላፊነቶች አሉባት። ሴት በመሆኗ፣ የሚሰጧት ኃላፊነቶችን የምትቀበለው ገና በትንሽ እድሜዋ ነው። አደግ ስትልማ በተለይ እንደሀገራችን ባሉ ያላደጉ ሀገሮች ላይ ኃላፊነቷ እየበዛ ነው የሚመጣው። ተፈጥሮ ከምትሰጣት ኃላፊነት ባሻገር ማኅበረሰቡ የሚያሸክማት ኃላፊነት አለ። ሲሆን ሲሆን ሴት ላይ የሚበዛውን ጫና ለመቀነስ ብዙ ጥረት ማድረግ፣ በብዙ መልኩ ማበረታታት ሲገባ እንዴት ፈቅዳ ባላመጣችው ነገር በተፈጥሮ ግዴታዋ መኖሯን እንድትጠላ ሴትነቷን እንድታማርር ይፈቀዳል ። ሴት ከፈጣሪ ድንቅ ስጦታ ተደርጎ በተሰጣት ነገር መማረር አይገባትም።

ሴት ልጅ የወር አበባ (menstruation) ማየት ጀመረች ማለት ፍሬያማነቷ ጀመረ ማለት ነው ። ልጅ የመውለድ ጸጋዋ ይጀምራል ማለት ነው። በዚህ ወርሐዊ ግዴታ ውስጥ ካላለፈች ልጅ ማግኘት አትችልም ። ይህ ድንቅ ስጦታ ነው። ይህን የምታሳልፍበትን ጊዜ መጥላት ሳይሆን በፈጣሪ ድንቅ ሥራ መደነቅ ነው የሚገባት። ለዚህ ደግሞ የምትኖርበት ማኅበረሰብ ነገሮችን ሊያመቻችላት እንጂ ነገሮችን ሊያከብድባት አይገባም።

በሚያሳዝን ሁኔታ ወደ ደቡብ ክልል ጂንካ ወረዳ ባሉ ገጠራማ አካባቢዎች ሴት ልጅ የወር አበባዋ ላይ ስትሆን፣ በጣም ትገለላለች ሰው ፊት እንድትቀርብ አይፈለግም። የበለጠ የሚያሳዝነው ደግሞ ይህንን የሚያደርጉት እናቶች ራሳቸው መሆናቸው ነው። እነሱም ያለፉበት የእነሱም የሕይወታቸው አካል ነው፣ ነገር ግን የሴት ልጅ የወር አበባዋ ሰዓት እንደ እርግማን ነው የሚቆጠረው። ተደብቃ እንድታሳልፍ ነው የሚደረገው። እነዚህ ሴቶች የወር አበባ፣ ልጅ ከመውለድ ጋር የሚያያዝ የተፈጥሮ ግዴታ እንደሆነ አይረዱም። ግንዛቤው የላቸውም። እነርሱ ልጆቻቸውን ያገኙት በዚህ ሂደት ውስጥ በማለፍ ነው ብለው አያስቡም።

በነገራችን ላይ በተለያዩ ገጠራማ የሀገራችን ክፍሎች ላይም ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸው ማኅበረሰቦች እንዳሉ ለማወቅ ችያለሁ። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍልም የዚህ አስተሳሰብ ተጠቂዎች መኖራቸውን በዛ አካባቢ መምህር በነበረበት ወቅት መታዘቡን አንድ ሰው አጫውተኝ። የሚያሳዝነው ነገር ሴቶቹ ልጆች የወር አበባቸው ላይ በሚሆኑበት ወቅት ይጸየፏቸዋል። ከቤተሰብ አባላት ጋር ማዕድ እንዲቀርቡ አይፈቀድላቸውም። ምግብ እንዲያዘጋጁ አይፈለግም ወደ ማዕድ ቤት እንዲገቡ እንኳን አያደርጓቸውም። ለብቻቸው የሚሆኑበት ጎጆም አላቸው። ምን ያህል ራሳቸውን ሊጠሉ እንደሚችሉ ነው የሚያሳየው። ይህ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው። ይህን አመለካከታቸውን የሚቀየር ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። ይህን ግንዛቤ ለመፍጠር ደግሞ በገጠራማው የአገራችን ክፍል የሚሠማሩ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና ከሴቶች ጋር በተያያዘ የሚሠሩ አካላት ትልቅ ሥራ መሥራት አለባቸው።

የጤና ባለሙያዋ ዶ/ር ኤልሳ ሙሉጌታ በዚህ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን ሲያካፍሉኝ ፣በተለያዩ አካባቢዎች በተለይ ደግሞ በገጠራማው የአገራችን ክፍል የሚገኙ ሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ሞዴስ ማግኘት ስለማይችሉ የተለያዩ ባዕድ ነገሮችን በመጠቀማቸው ምክንያት ለተለያዩ የማህጸን በሽታዎች ተጋላጭ የሚሆኑበት አጋጣሚ ሰፊ እንደሆነ ነግረውኛል። ከዓመታት በፊት ይሠሩበት ወደነበረው በአማራ ክልል አገው ዞን በሚገኝ አንድ የገጠር ሆስፒታል ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ብዙ ሴቶች በማህጸን ኢንፌክሽን፣ በማህጸን ፈንገስ፣ በተለያዩ የማህጸን አለርጂዎች፣ ተጠቅተው ይመጡ እንደነበር አስታውሰዋል።

ወደ ሆስፒታሉ የሚመጡት ሴቶች የንጽሕና መጠበቂያ ማግኘት አይችሉም። በዚህም ሳቢያ ንጹሕ ያልሆነ ስፖንጅ (ስፖንጅ ከተገኘ ነው) በኩበት፤ በአፈር ይጠቀማሉ። መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ተገቢውን ትኩረት መስጠት አለባቸው። ምክንያቱም ሴት ልጅ ሀገር ናት በአንድ አገር ላይ የሴት ልጅ ድርሻ በጣም ጉልህ ነው። ነገር ግን እንክብካቤ ቀርቶ፣ ይህንን የተፈጥሮ ግዴታዋን እንኳን መቋቋም የምትችልበት ነገር ሊመቻችላት ይገባል ብለዋል።

ዶ/ር ኤልሳ አክለውም ወደ ቤተሰቤ አዲስ አበባ በምመጣበት ወቅት የራሴን እንዲሁም ከተለያዩ ሰዎችና ድርጅቶች የሰበሰብኩትን ንጽህና መጠበቂያ ሞዴስ ይዤ ነበር የምመለሰው። ሁሉን ማዳረስ የማይቻል ቢሆንም ወስጄ ለሴት ተማሪዎች ነበር የማከፋፍላቸው። ይሄ ዘላቂ መፍትሔ እንዳልሆነ ባውቅም፣ ጉዳዩ በጣም ያሳስበኝና ያስጨንቀኝ ስለነበር ለጥቂት ግዜ የሚሆናቸውን ይዤላቸው እሄድ ነበር። ከዛ አካባቢ ሥራ ከለቀቅኩ በኋላም ቢሆን ለተወሰነ ግዜ ያህል ከዚህም፣ ከሀገር ውጪ ያሉ ሰዎችም ጭምር እንዲያግዙኝ በማድረግ እያሰባሰብኩ እልክላቸው ነበር። ከዛ በኋላ ግን ከአቅሜ በላይ በመሆኑ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ሲሉ ዶ/ር ኤልሳ ባዘነ መንፈስ ውስጥ ሆነው አጫውተውኛል።

በእርግጥም ጉዳዩ በጣም የሚያሳዝን ነው። እነዚህ በገጠር ያሉ ሴቶች እንዴት ጠንካሮች ናቸው ስል አሰብኩ። በከተማ ያለን ሴቶች እንኳን ነገሮች ተመቻችተውልን፣ ቢወደድም የንጽሕና መጠበቂያውን እያገኘን በተፈጥሯዊ ሕመሙ ምክንያት፣ ምን ያህል ከባድ ጊዜ እንደምናሳልፍ አውቃለሁ። የወር አበባ በባህሪው የራሱ ሕመሞች አሉት ራስ ምታት፣ የሆድ ቁርጠት የተለያዩ እንደዚሕ ናቸው ተብለው ሊገለጹ የማይችሉ ስሜቶች አሉት። ታዲያ እነዚህ ሴቶች በዚህ ሕመምና ባልተመቸ ሁኔታ ውስጥ ሆነው፣ የሚያሳልፉትን ስቃይ ማሰቡ በራሱ ከበደኝ። ይህን ጉዳይ ለመረዳት ከወንድ ይልቅ ለሴት ይቀላልና የሴቶች ጉዳይ እና ከሴቶች ጋር በተያያዘ የሚሠሩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በአንክሮ ሊመለከቱትና ችግሩን መፍታት ለሚችለውም አካልም ትኩረት እንዲሰጠው የማድረጉን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት አለባቸው።

> **ሴት ልጅ ሀገር ናት በሀገር ግንባታ ውስጥ የሴት ልጅ አበርክቶ ትልቅ ነው። አገር ከቤተሰብ ይጀምራል በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ደግሞ ቤተሰቡን በማቆም ዙሪያ የሴቷ ሚና እጅግ የጎላ ነው**

አሁን ደግሞ ዋጋው፣ አይደለም በገጠር ያሉት በከተማ ያሉ እህቶች እንኳን መግዛት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሷል። በምኖርበት አካባቢ የአትክልት ችርቻሮ በመሸጥ የምትተዳደርን አንዲት እህት ስለ ጉዳዩ ስጠይቃት የነገረችኝን ላካፍላችሁ። ሞዴስ ገዝቼ መጠቀም አቁሜያለሁ። ዋጋው ከእኔ አቅም በላይ ነው። እኔ ደግሞ አንድ እሽግ ብቻ አይበቃኝም ሁለት እሽግ ነው የምጠቀመው። ይህን ለመግዛት ደግሞ አሁን ካለው የኑሮ ውድነት ጋር አቅሜ አይፈቅድም። በመሆኑም ጨርቅ እያጠብኩ መጠቀምን እንደ አማራጭ ወስጄዋለሁ አለችኝ።

በገጠር ካሉ ባእድ ነገር ከሚጠቀሙት በአንጻራዊነት ይሻላል። እሷ ሳሙና እና ውሃ የማግኘት እድል ስላላት፣ የሚመከር ባይሆንም ኩበትና ቃጫ ከመጠቀም ይሻላልና ጨርቅ እያጠበች መጠቀምን አማራጭ አደረገች። ውሃና ሳሙና በበቂ ሁኔታ ማግኘት የማይችሉትስ አማራጫቸው ምንድነው?። ሌሎችም ያነጋገርኳቸው ሴት እህቶች የዋጋው በዚህ ደረጃ መጨመር እንዳስመረራቸው ነገር ግን ግዴታ ስለሆነ እያዘኑም ቢሆን እንደሚገዙ ነግረውኛል።

ከዓመታት በፊት በትግራይ ክልል እያጠቡ ለመጠቀም የሚያስችል የንጽህና መጠበቂያ ሞዴስ የፈጠራ ሥራ የሠራች ሴት ነበረች። ይህም ሌላ የተሻለ አማራጭ ነው። ንጽሕና መጠበቂያው አንድ ጊዜ ገዝተው ለረጅም ጊዜ እያጠቡ በመጠቀም በየወሩ ከሚወጣ ወጪ ሴቶችን የሚገላግል የፈጠራ ሥራ ነበር። ወደተለያዩ አካባቢዎች የመድረስ እድል ባያገኝም። ነገር ግን ሞዴሱን ለመሥራት የሚያስፈልግ ጥሬ እቃ አቅርቦት እጥረት እንዲሁም፣ ምርትን ለማምረት በሚደረገው ሂደት ውስጥ የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች አለማግኘት፣ የካፒታል እጥረት፣ የቦታ ማጣት፣ ምርትን ለማከፋፈል አመቺ ሁኔታ አለመኖር፣ የመሳሰሉ ችግሮች ቢኖሩበትም የተወሰነ ምርት በማምረት ማሳያውን የተወሰነ ቦታ ለማቅረብ የተሞከረበት አጋጣሚ ነበር። ምርቱም በጣም ተፈላጊ ሆኖ ነበር። ነገር ግን ከላይ በጠቀስኳቸው ምክንያቶች እና የሚያግዝ አካልም በማጣት ማምረት መቀጠል አልተቻለም። እነዚህን ነገሮች ማመቻቸትና ምርቱን የማስቀጠል ሥራ ቢሠራ ኖሮ በተወሰነ መልኩ ችግሩን ማቃለል ይቻል ነበር።

ሴት ልጅ ሀገር ናት በሀገር ግንባታ ውስጥ የሴት ልጅ አበርክቶ ትልቅ ነው። አገር ከቤተሰብ ይጀምራል በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ደግሞ ቤተሰቡን በማቆም ዙሪያ የሴቷ ሚና እጅግ የጎላ ነው። ጠንካራ ሀገር እንዲኖረን ጠንካራ ቤተሰብ መገንባት አለብን። ጠንካራ ቤተሰብ ለመመሥረት ደግሞ በሁሉም ዙሪያ ጠንካራ ሴት ታስፈልገናለች። ታዲያ ይህቺ ሴት የቤተሰቧ ምሰሶ ሆና እያለ በተፈጥሮ የሚሰጣትን ስጦታ፤ መሠረታዊ ነገሯን መቋቋም የምትችልበት ነገር ማግኘት የተአምር ያህል እንዴት ሩቅ ይሆንባታል።

በመጨረሻም የጉዳዩ ባለቤት እንደሆነችና በጣም እንደሚሰማት አንዲት እንስት ቢደረግ የሚል ሃሳቤን አቅርቤ ልደምድም። እንደ መንግሥትና ባለድርሻ አካላት የጉዳዩን ክብደት ሊገነዘቡት ይገባል ። የሴቶች የንጽሕና መጠበቂያ ሞዴስ ምርቶች ላይ ያለ ታክስ ሊነሳ ይገባዋል። ይህ የተፈጥሮ ግዴታ ነው እንደ መብላት፣ እንደ መጠጣት ለሴት ልጅ ግዴታ ተደርጎ ከፈጣሪ የተሰጣት ነው። **ሰላም!**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## "ኢንሳ በደራሽ ፕላትፎርም ቴክኖሎጂ ፈር ቀዳጅ ስራ እየከወነ ነው"

**- የኢንሳ የተቀናጀ ፕላትፎርም ዲቪዚዮን ዳይሬክተር አቶ ብሩክ ገብረየስ**

**ዳግም ከበደ**

ጉዳይ ኖሮን ወደ አንድ የመንግስትም ሆነ የግል ተቋም ስንሄድ በቅድሚያ የሚያሳስበን ወረፋ ጥበቃ እና እንግልቱ ነው። ጊዜያችንን የሚያቃጥለው ወረፋ እንዳይገጥመን፣ እንግልት እንዳይደርስብን ብለንም መረጃ የሚያደርሰን ወይም ጉዳዩን ለማስፈጸም የሚተባበረንን ሰው ፍለጋ እስከ መማሰን እንደርሳለን።

ይህ ተግዳሮት በመንግስት አገልግሎት ሰጪዎች ተቋማት ወይም የክፍያ ቦታዎች በስፋት ያጋጥማል። በግብር ክፍያ፣ በንብረት ማዘዋወር፣ በፈቃድ እድሳትና በመሳሰሉት ቀና አሰራሮች ባለመኖራቸው ሳቢያ ባለጉዳዮች ጉዳያቸውን ለማስፈጸም ሲቸገሩ ኖረዋል፡፡

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ሀገሮች ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅ ተግብረዋል፡፡ ጊዜን ለመቆጠብ፣ ከአላስላጊ ወጪ ለመዳን እንግልትን ለማስቀረት የሚያስችሉ ጉዳዮች በፍጥነት እንዲከወኑ የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎችና የክፍያ ስርዓቶች ስራ ላይ በመዋላቸውም ጉዳዩ በፍጥነት እና ያለምንም እንግልት የሚፈጸምበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡ ፡ በአሰራር ስርዓት ችግር ሳቢያ የሚፈጥረውን እንግልት የሚቀንሱ ተገቢ ያልሆነ ወጪን የሚቆጥቡ፣ ጊዜን የሚቆጥቡ ፕላትፎርሞች፣ መተግበሪያዎችና ሲስተሞች የዘመኑ አማራጮች በመሆን ተመራጭነታቸው እየሰፋ መጥቷል።

ይህን መሰል ዲጂታል አገልግሎት በአገራችን እምብዛም ሳይታወቅ ቆይቷል። በአሁኑ ወቅትም ጥሩ የሚባሉ ሙከራዎች ቢኖሩም፣ አሁንም ቴክኖሎጂውን ለማበልፀግ የሚሰሩ ተቋማት ብዙም አይታዩም።

በርካታ ገንዘብ ሰብሳቢ ተቋማት አሁንም ስራዎቻቸው በእጅ አሠራር/ በማንዋል/ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ደንበኞቻቸው ክፍያ ለመፈጸም በአካል እንዲቀርቡ ያደርጋሉ። ይህ አይነቱ አሰራር በሁለቱም ወገን በኩል ብዙ ችግሮችን አስከትሏል። ምክንያቱም ተገልጋዮች የግድ አገልግሎት ሰጪዎች ቢሮ ወይም አገልግሎት መስጫ ማእከል መሄድ ይኖርባቸዋል፤ በእዚያም ሄደው ለፍጆታ፣ ለግብር እና ለሌሎች አገልግሎቶች ሂሳባቸውን ለመክፈል ረጅም ወረፋ ይጠብቃሉ። አንዳንድ ጊዜ የኢንተርኔት ግንኙነት ባለመኖር፣ በመብራት መቆራረጥ ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ባሉ ሌሎች ችግሮች ሳቢያ አገልግሎቱን በብቃት ማግኘት አይችሉም።

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢንሳ) ባለቤትነት "ደራሽ" የተሰኘ ፕላትፎርም (የክፍያ ደረሰኞችን ለባንኮች ተደራሽ የሚያደርግ መድረክ) ተዘጋጅቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል። ይሁን እንጂ ይሄም ፕላትፎርም በሚፈለገው ደረጃ አይታወቅም። ለመሆኑ ፕላትፎርሙ ምን ይዘት አለው? በምን መንገድ ይሰራል? እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን የኢንሳ የተቀናጀ ፕላትፎርም ዲቪዚዮን ዳይሬክተር ከሆነው አቶ ብሩክ ገብረየስ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ ይዘን ቀርበናል። መልካም ቆይታ!

**አዲስ ዘመን፡- "ደራሽ" የተሰኘው ፕላትፎርም በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በልፅጎ ተግባር ላይ ውሏል። ፕላትፎርሙ በምን መንገድ ይሰራል?**

**አቶ ብሩክ፡-** "ደራሽ" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢንሳ) ባለቤት የሆነበት በአገር ውስጥ የለማ ፕላትፎርም ነው። ፕላትፎርሙ የክፍያ አማራጭ ሳይሆን ለክፍያ አገልግሎት የሚሆን ደረሰኝ በዲጂታል አማራጭ ማቅረብ "bill aggregations" ነው። ይህ ማለት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለክፍያ የሚጠቀሙበትንደረሰኝ በደራሽ አማካኝነት እንዲቀርብ ይደረጋል። ባንኮች ደግሞ



የቀረበውን ደረሰኝ "Bill Presentment" ተጠቅመው ያለምንም መጉላላት ከዚያ ላይ በመውሰድ ክፍያ እንዲፈፅሙ ይቀርባል። ይህ ፕላትፎርም የሞባይል አፕሊኬሽን (መተግበሪያ)፣ ዌብሳይትና ሲስተምን "Application Programming Interface" አካትቶ የሚሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የደራሽ ፕላትፎርም ስራ ላይ ከዋለ ምን ያህል ጊዜ ሆነው? ደህንነቱስ ምን ያህል አስተማማኝ ነው?**

**አቶ ብሩክ፡-** የተቀናጀ የደራሽ ፕላትፎርም አገልግሎት ላይ መዋል ከጀመረ አራት ዓመታትን አስቆጥሯል። በኢንሳ ባለቤትነት ይሁን እንጂ በአገር ውስጥ ከሚገኝ ተቋም ጋር በትብብር የለማ ነው። የሚያስተዳድረውና በባለቤትነት የያዘውም ኢንሳ ነው። ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ የተደረገ ነው። የፍቃድና አላስፈላጊ ወጪ እንዳይኖርበትም ተደርጓል።

በኦላይን አማራጭ ደራሽን የመሰሉ ፕላትፎርሞች ለአገልግሎት ሲቀርቡ ብዙ አይነት አደጋን ሊያስከትሉ የሚችሉ አካላት ያጋጥማሉ። ይህን መሰል አገልግሎት በበይነ መረብ እስካቀረብክ ድረስ ተጋላጭነትህም ሰፊ ነው የሚሆነው። በተለይ ከፋይናንስ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው ከሆነ ለጥቃት የመዳረግ ሁኔታው ከፍተኛ ነው።

ይህን መሰል ፕሮግራሞችን ለማጥቃት ፍላጎት ያላቸው አካላትም በስፋት በዓለማችን ላይ አሉ። ይህን ጥቃት ለመከላከል ፕላትፎርሙን ዲዛይን ከማድረግ ጀምሮ ሊሰነዘሩ የሚችሉ ጥቃቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ታስቦ ነው የሚሰራው። ስለዚህ ከስራቱ ጀምሮ ይህን ታሳቢ በማድረግ ነው ደራሽ የተሰራው። በተለይ የባንክ መረጃን (አካውንትን) እንዳይዝ ተደርጎ የተሰራ ነው።

በተለይ የግብር ክፍያን በተመለከተ ባንኮች ራሳቸው በደራሽ ፕላትፎርም መረጃ ሲያስተላልፉ ገንዘብ አይልኩም። ይህ አይነት አሰራር መኖሩ ለጥቃት በቀላሉ ተጋላጭ እንዳይሆን አድርጎታል። ከዚህ ውጪ ዓለም ላይ ያሉ የጥቃት መከላከያ ስርዓቶች በሙሉ ተተግብረውበታል። ይህ ደግሞ የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን አስችሎታል።

ይህን መሰል ፕላትፎርም በአገር አቀፍ ደረጃ ባንኮች ላይ ያለውን መሰረተ ልማት የተገበሩ አገራት ጥቂት ናቸው። በየጊዜው የሳይበር ጥቃት ትራፊኩን በመከታተል ጥቃት እንዳይደርስ ይሰራል። ይህን መከታተል ካልተቻለ ሰርገው የሚገቡ ጥቃት አድራሾች ተጠቃሚዎች በአግባቡ እንዳይገለገሉ አገልግሎቱን የማቋረረጥ ስራ ሊሰሩ እንደሚችሉ ይጠበቃል። ይህ እንዳይሆን ጥቃቱን የሚከታተልና የሚከላከል ቡድን ለደራሽ በልዩ ሁኔታ ተዋቅሮ እየሰራ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- አገልግሎት መስጠት ከጀመረ አራት ዓመታትን ያስቆጠረው የተቀናጀ የደራሽ ፕላትፎርም እስካሁን ድረስ ከሳይበር ደህንነት አንፃር ያጋጠመው ጉዳት ይኖር ይሆን?**

**አቶ ብሩክ፡-** በየቀኑ በጣም ብዙ ሙከራዎች አሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ፕላትፎርሙ ላይ አደጋ ያደረሱ እስካሁን አልተመዘገቡም። ከአሰራር ጉድለትና ከግንዛቤ ጉድለት አንፃር አገልግሎቱ የተቀቆራረጠበት አጋጣሚ ተፈጥሮ ሊሆን ይችላል። ይሄ ራሱ እንደ ደህንነት ስጋት ችግር ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ይሁን እንጂ የውጪ ጥቃት ግን እስካሁን ድረስ አላጋጠመንም። በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ሙከራዎች ግን አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ደረሰኞችን ለባንኮች በማቅረብና የክፍያ ስርዓት በማቅለል የሚሰሩ ሌሎች ፕላትፎርሞች በአገር ውስጥ አሉ? እንደ ደራሽ ያሉ ዲጂታል ፕላትፎርሞች ከሌሎች ዲጂታል አገልግሎቶች በምን ይለያሉ?**

**አቶ ብሩክ፡-** በመጀመሪያ ፕላትፎርም ምንድነው የሚለውን ነገር መረዳት ያስፈልጋል። ፕላትፎርምና ሲስተም የተለያዩ ናቸው። ሲስተም በአንድ ጎን ብቻ አቅራቢ ኖሮት ተጠቃሚዎችን ብቻ የሚያካትት ሲሆን ነው። ድረ ገፅ፣ ፖርታሎች፣ መተግበሪያዎችና ሌሎች አማራጮችም ሊሆኑ ይችላሉ።

ፕላትፎርም ስንል ግን ብዛት ያላቸው ተሳታፊዎችን የሚያካትት ነው። ለምሳሌ ፌስቡክን ፕላትፎርም ያስባለው እዚያ ውስጥ የተለያዩ ወገኖች በጋራ ተሳትፎ ማድረጋቸው ነው። እነዚህን አካላት ማገናኘት ሲቻልና ደንበኞች በዚያ ውስጥ ሲገለገሉ ፕላትፎርም ይሆናል። የዩቱብ፣ አሊባባ፣ አማዞን ፕላትፎርም የሚያስብላቸው በውስጣቸው አንዱ አቅራቢ ሌላኛው ደግሞ ተጠቃሚ ስለሚሆንና ተሳታፊዎቹ ብዛት ያላቸው "multisided" አሊያም "two-sided" የሚያገናኙ ስለሆኑ ጭምር ነው።

ከዚህ አንፃር አገልግሎት ሰጪና ባንኮችን በነፃነት፣ በቀላሉ ገብተው ሊሳተፉበት የሚችሉበት አሊያም ደግሞ ለረጅም ጊዜ የሰራ አስተማማኝ የሆነ ፕላትፎርም አገር ውስጥ አለ ብዬ አላስብም። ወደዚህ ለመድረስና መሰል የዲጂታል አማራጮችን ለማቅረብ እየሞከሩ ያሉና የተለያዩ መነሻዎች ግን አሉ። ጅማሮዎች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ፕላትፎርምና የኢኮኖሚ ስርዓቱ በምን መልኩ መስተጋብር አላቸው ብለህ ታምናለህ። ከዚህ አኳያ የደራሽ ሚና ምንድነው?**

**አቶ ብሩክ፡-** በአሁኑ ወቅት የአገራት ኢኮኖሚ ወደ ፕላትፎርም ኩባንያዎች ዞሯል። ለምሳሌ የፌስቡኮችን ፕላትፎርምን ማየት ብንችል አመታዊ ትርፋቸው ከአንድ አገር ሃብትና በጀት ጋር የሚስተካከል እየሆነ ነው። የእነ ጎግል እና ሌሎች ፕላትፎርሞችም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው። አለምን እየመራው ያለው ይህ ኢኮኖሚ መርህ በመሆኑም መንግስታት በዚህ ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ሙከራ እያደረጉ ይገኛሉ።

ኢንሳም ይህንን በመረዳት ደራሽ ፕላትፎርምን አበልጽጎ ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ ላይ እየሰራ ይገኛል። አንደኛው ስራው በመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ያለውን የአሰራር ስርዓት በዲጂታል አማራጭ እንዲቀል የማድረግ ስራን መስራት ነው። በሁለተኛ ደረጃ በአብዛኛው የገንዘብና የመረጃ ዝውውር የሚደረገው ይህን በመሰለው ፕላትፎርም ስለሆነ ይህንን በባለቤትነት መቆጣጠር፣ ማስተዳደር እንዲሁም ደህንነታቸውን መጠበቅ ከተቻለ በቀጣይ ዜጎች ወደ እነዚህ አገግልግሎትና ቴክኖሎጂ ባለቤትነት እንዲሄዱ ፈር ቀዳጅ የመሆን ስራ መከወን ነው። ከዚህ አንፃር ኢንሳ ኢኮኖሚውንም ሆነ የደህንነቱን ጉዳይ በማቀናጀት ፈር ቀዳጅ ለመሆን እየሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ደራሽን ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ ከማሻሻልና አዳዲስ የአገልግሎት አማራጮች እንዲኖሩት ከማዘመን አንፃርስ ምን ሰርታችኋል?**

**አቶ ብሩክ፡- አሁን የመጀመሪያው የተደራሽነት ስራ ላይ እየሰራን** ነው። ያለውን ፕላትፎርም በአግባቡ እንዲጠቀሙበት የማድረግ ስራ እየተከናወነ ነው። ወደ ማሻሻል የመግባቱን ስራ ተጠቃሚዎች ያላቸው የመሰረተ ልማት አቅም ይወስነዋል። በተጠቃሚዎች ፍላጎትና ጥያቄ መሰረት ነው የማሻሻል ስራ የሚካሄደው። አሁን እያደረግን ያለነው ባንኮች በቅርንጫፍም በኢንተርኔትም አገልግሎት ሰጪዎች አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ስራ ነው። ከዚያ ውጪ ግን የሞባይል መተግበሪያ (አፕሊኬሽን) ተዘጋጅቶ በሙከራ ደረጃ ላይ ይገኛል። በቅርቡም የውሃ፣ የመብራትና ሌሎች የክፍያ ደረሰኞችን ወዳጅ ዘመዶች ለቤተሰቦቻቸው ከውጪ ሆነው ካሉበት ስፍራ መክፈል እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች ተጀምረዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በደራሽ ፕላትፎርም ተጠቃሚ የሆኑ ምን ያህል ደንበኞች አሏችሁ? በዚህ ዲጂታል ስርዓት ለመጠቀም ያላቸው ተነሳሽነትስ ምን ይመስላል?**

**አቶ ብሩክ፡-** አሁን ባለው ሁኔታ 16 ባንኮች ተሳስረዋል። ተጨማሪ አራት ባንኮችም በዚህ ወር ወደ አገልግሎት እየገቡ ነው።

በአገልግሎቱ እንዲጠቀሙ የማድረጉ ስራ ትልቅ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል። በመሆኑም የማለማመድ፣ ማሳመንና አገልግሎታቸውን በዚህ አግባብ እንዲሰጡ ማስቻል ራሱን የቻለ ስራ የሚፈልግ ነው። ያንን በመስራት ላይ እንገኛለን። ከአንዱ ወደ ሌላኛው ባንክ የሚደረግ የደረሰኝ ክፍያን የብሄራዊ ባንክ ህግና አሰራር ቢፈቅድም ባንኮች ገንዘብ ከራሳቸው እንዳይወጣ ስለሚፈልጉ ፍቃደኛ አለመሆን ይታይባቸዋል። አሁን ግን በተለይ የግብር ክፍያ ከየትኛውም ባንክ ወደ ንግድ ባንክ መክፈል እንዲቻል ተደርጓል። ሌሎችም የትራፊክ፣ የውሃና መሰል የክፍያ ስርዓቶች በዚህ ፕላትፎርም እንዲከፈሉ ማድረግና ማሻሻል ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- በተቀናጀ የደራሽ ፕላትፎርም እስካሁን ድረስ ምን ያህል የደረሰኝ አቅርቦትና የገንዘብ ክፍያ ተደርጓል?**

**አቶ ብሩክ፡-** በመጀመሪያው ዓመት ላይ በግብር ከፋዩ ነበር የጀመርነው። 10 ከፍተኛ የመንግስት ግብር ከፋዮችን ሃላፊነት ተወስዶ ከንግድ ባንክ እንዲከፍሉ ለማድረግ ተሞክሮ ነበር። ይህን ያደረግነውም በስንት ጥረት አመኔታ ለማሳደር ተብሎ ነው። ወደ ስርዓቱ ለማስገባት አንድ አመት ያህል ፈጅቷል። ሆኖም በቀጣይ በተሰራው ስራ ወደ 5 እና 6 ሺህ ለማስገባት ተችሏል። በዚያ ወቅት ከ5 እስከ 10 ቢሊዮን ብር ክፍያ ተፈፅሟል።

ከዚያ በኋላ ባለው ከሰኔ ጀምሮ ተጨማሪ 6 ባንኮች ተካተውና አገልግሎት ሰጪዎችም ወደ 50 ተጠግተው በሲቢኢ ብርና በሌሎች አማራጮች ወደ 70 ቢሊዮን ብር የደረሰኝ ክፍያዎች ተከፍለዋል። ይህ ማለት ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከነበረው ሁለት እጥፍ በአንድ ዓመት ውስጥ መጥቷል። አጠቃላይ ሲስተሙ ላይ ክፍያ የፈፀሙና የሚጠቀሙ ወደ 450 ሺህ በላይ ተጠቃሚዎች አሉ። ከዚህ ውጪ 65 የሚደርሱ አገልግሎት ሰጪዎች በደራሽ የተቀናጀ ፕላትፎርም ለደንበኞቻቸው በዲጂታል አማራጮች ተጠቃሚ እየሆኑ ነው። ይህን በወር ሲሲሰላ እስከ 70 ሺ ተጠቃሚዎች ይደርሳሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለጡን ሰፊ ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**አቶ ብሩክ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃዎች የሀገር ሕልውና ስጋቶች

**አልማዝ አያሌው**

የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ በሀገር ሕልውና እና በሕዝቡ ደህንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ነው። በሚሰራጩ ሐሰተኛ ዘገባዎች ሰዎች በማንነታቸው እንዲሁም በሚከተሉት እምነታቸው ጥቃት እየደረሰባቸው ይገኛል። በመሆኑም የጥላቻ ንግግር እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ተፈጻሚ መሆን አለበት የሚሉ አስተያየቶች በርክተዋል። በሌላ በኩል የሕጉ ተፈጻሚነት የመናገር መብትን እንዳይገድብ ያሰጋል የሚል አስተያየት የሚያነሱም አልጠፉም ።

የጥላቻ ንግግር እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አዋጅ ቁጥር 1185/2012 ወጥቷል። አዋጁ የወጣው ሆን ተብሎ የሚሰራጩ የጥላቻና ሐሰተኛ ንግግሮችን በሕግ መከላከልና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው። በአዋጁ ላይ እንደተመላከተው የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ለማኅበራዊ ስምረት፣ ለፖለቲካ መረጋጋት፤ ለሀገራዊ አንድነት፣ ለሰብዓዊ ክብር እና ለእኩልነት ጠንቅ መሆኑን በመገንዘብ ነው። እንዲሁም መሠረታዊ መብቶች ላይ የሚጣሉ ገደቦች በሕግ የተደነገጉ፣ በዲሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆነ ተመጣጣኝና በጠባቡ የተበጁ መሆን እንዳለባቸው በመገንዘብ ነው ይላል።

የፋክት ቼክ መሪ የመረጃ አጣሪ ወይዘሪት ረሆቦት አያሌው በሰጡት አስተያየት፤ ሰዎች በነጻነት ያለገደብ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ይፈለጋል። ይሁን እንጂ ሰዎች በመረጃና ማስረጃ በልምድ ላይ ተመርኩዘው ሳይሆን በስሜትና ስሜት ቀስቃሽ በሆኑ ንግግሮች ሀሳባቸውን ይገልጻሉ። የኅብረተሰቡን የአኗኗር ባህል የሚሸረሽሩ የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃዎች በተለያየ መንገድ ይተላለፋሉ። ይሄ በተለይ በአሁኑ ወቅት ትልቅ ፈተና ሆኗል። ሐሰተኛ መረጃዎች በተለይ በስፋት የሚሰራጩት በዩቲዩውብ፣ በቲውተር፣ በቴሌግራም እና በኢንስታግራም ነው። በሌሎች እንደ ቲክ ቶክ ባሉት የመገናኛ ዘዴዎች ይተላለፋሉ። በመሆኑም ኅብረተሰቡ ይህን መረዳት አለበት። የሚያገኛቸውን መረጃዎችም ለራሱም ሆነ ለሌሎች ከማሰራጨቱ በፊት እውነታውን ማወቅ አለበት። ያገኛቸውን መረጃዎች ሁሉ ከማሰራጨት መቆጠብ ይኖርበታል። በሁሉም የመገናኛ ብዙኃን እና የበይነ መረብ የሚተላለፉ መረጃዎች እውነተኛ ናቸው ብሎ ከመውሰድ መቆጠብ ያስፈልጋል።

አሁን ያለንበት የቴክኖሎጂ ዘመን ነው። ቴክኖሎጂው በስፋትና በብዛት ኅብረተሰቡ ጋር ይደርሳል። ለምሳሌ በሀገራችን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚው ቁጥር 25 በመቶ ደርሷል። ይሄ ቁጥር ካለፈው ዓመት ጋር ሲተያይ ዘንድሮ የአምስት በመቶ ብልጫ አሳይቷል። ይሄ ማለት እስማርት ስልኮችን በመጠቀም ኅብረተሰቡ በቀላሉ እጁ ላይ መረጃዎችን ያገኛል ማለት ነው። የማኅበራዊ ትስስር ገጾች ደግሞ በሕዝቡ ተቀባይነት አላቸው ። በመሆኑም የተገኘው መረጃ ሁሉ ትክክል መሆን አለመሆኑን ማጣራት እንደሚያስፈልግ የመረጃ ማጣራት ባለሙያዋ ይናገራሉ።

ሌላው አስተያየታቸውን የሰጡት የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንትና የአህዱ ሬዲዮ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ ናቸው። እርሳቸው እንዳሉት የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ ከሚሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ አሁን ከብሔርና ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ ወገንተኝነትን ይዘው በተቋቋሙ መገናኛ ብዙኃን ነው። እነዚህ መገናኛ ብዙኃን የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ይዘው የተፈጠሩ ናቸው። ቀደም ሲል የነበሩት ደግሞ ወደ አንድ የመንግሥት ጎን ያደሉ ናቸው።

አሁን ላለንበት ሁኔታ ሌላው ችግር ቀደም ሲል የተፃፉ ታሪኮች፣ ፊልሞች እና መሰል ነገሮች ናቸው። በባህላችን በብዙ መጽሐፍት የተጻፉትን ፣ሙዚቃዎች የግጭት መነሻ አድርገዋል። ብዙ የኢትዮጵያ ታሪክ እና ባህል የተጻፈውም በውጪ ጸሐፍት ነው። ስለዚህ ባህሎቻችንና ታሪኮቻችን መታየት አለባቸው ሲሉ ጋዜጠኛ ጥበቡ ይጠቅሳሉ። ባለፉት 25 ዓመታት ጋዜጠኞች ታስረው የነበረው በፃፉት ውሸት ሳይሆን በሠሩት እውነት ነበር ሲሉ ይሞግታሉ። አሁን ደግሞ በመደበኛ ሚዲያዎችም ቢሆን ባለስልጣናት የሚናገራቸው ከፍተኛ የጥላቻ መርዝ ያለባቸው ንግግሮች የሚተላለፉበት ሁኔታ አለ። ይሄም ቢሆን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚል እምነት አላቸው።

በፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ የሕግ ጥናትና ማርቀቅ ዳይሬክተር ጀነራል አቶ በላይሁን ይርጋ እንዳሉት፤ ለሰው ልጆች ከተሰጡት መብቶች መካከል የመጀመሪያው ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ነው። ይሄ ያለገደብ የሚፈጸም መብት ነው። ሆኖም ግን በልዩ ልዩ ሁኔታ ያለ ገደብ ሀሳብን መግለጽ ሊያደርሰው ከሚገባ ጉዳት አንጻር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ሊገደብ ይችላል። ክብረ ነክ፣ ባለስልጣናት ላይ ጥርጣሬ እንዲኖር የሚያደርግ፣ ጥላቻን የሚያሰፋ፣ አንዱን ሃይማኖት በሌላው ላይ የሚያነሳሳ ፣ አንዱን ብሔር ከሌላው ጋር የሚያጋጭ እንዳይሆን በመጠኑ በሕግ ገደብ ሊጣልበት ይገባል።

ለምሳሌ በጀርመን ሀገር ሂትለር በአይሁዶች ላይ ከነበረው ጥላቻ በመነሳት በርካቶች እንዲገደሉ ተደርጓል። ሰዎቹ እንዲሞቱ ከመደረጉም በላይ በሰውነታቸው ውስጥ ያለው ስብ ተወስዶ ሳሙና እንዲሠራበት ሆኗል። ይሄ እጅግ ከሰብዓዊነት የወጣና ጭካኔ የተሞላው ዘግናኝ ድርጊት ነው።

እንዲሁም በሩዋንዳ በቱትሲ እና ሁቱ ጎሳዎች መካከል የተፈጠረው የእርስ በእርስ የዘር ማጥፋት ዘመቻ በበርካታ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ሕይወት ጠፍቷል። ይሄ በታሪክ ተመዝግቦ ያለ ነው። በሀገራችንም በተለያየ ከማንነትና ከሃይማኖት ጋር ተያይዞ የተፈጸሙ ክስተቶች አሉ። ይሄ ከሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ክስተት ነው፤ ሀገራችንም ችግሩን በዚህ መልኩ ካልተቀበለችውና የሕግ ተጠያቂነት ካልሰፈነ ችግሩ የከፋ ደረጃ ላይ ይደርሳል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ እየተለማመደችው ባለው አዲስ የዴሞክራሲ ሥርዓት ጽንፈኝነትና አሸባሪነት ጎልቶ እየታየ መምጣቱን አንስተዋል። በዚህ የዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የሚስተዋለው ውጥረት «አዲሱ ተለምዶ» መሆኑን ያሳያል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ከመረጃ ቴክኖሎጂ በኋላ ድህረ እውነትና አዲስ የዴሞክራሲ ልምምድ እያደረገች ትገኛለች። በዚህም ሁኔታ እንደ ፖለቲከኛ፣ አክቲቪስትና ማኅበራዊ ሚዲያ ያሉ የተከፋፈሉ ኃይሎች ተፈጥረዋል። ይህ ለአገሪቷ አዲሱ ተለምዶ ሲሆን፣ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችና ውጥረቶችም በአዲሱ የዴሞክራሲ ሥርዓት የተፈጠሩ ናቸው። ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ እነዚህ እውነታዎች የሉም፤ በዚህ የልበ ሰፊነት የዴሞክራሲ ልምምድ ውስጥ ሐሰተኛ መረጃዎች መስፋፋት ችለዋል።

በኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃዎች ስርጭት ለፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ለአገራዊ አንድነትና ለሰብዓዊ ክብር ጠንቅ በመሆናቸው፤ የሐሰት መረጃንና ጥላቻ ንግግር የሚያሰራጩትን መቆጣጠር አስፈላጊም እና ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን አስምረውበታል።

በሀገራችን የቴክኖሎጂ መስፋፋት አለ። የቴክኖሎጂ እድገቱ ትክክለኛ መረጃ ከማግኘት ይልቅ ስሜት ኮርኳሪና ሐሰተኛ መረጃዎች እንዲበዙ በር ከፍቷል። ይህንን በመታገልና የመረጃዎችን እውነትነት በመመርመር ጠንካራ አገር መፍጠር ይገባል ሲል ነው የተከራከሩት።

አሁን ያለንበትን ምህዳር መረዳት ያስፈልጋል፤ ሐሰተኛ መረጃ ዓለምአቀፋዊ ነው። አንዳንዴ በዲጂታል ቴክኖሎጂው ከውጪ የሚመጡ መረጃዎች አሉ። ዓለምአቀፉን ማኅበረሰብ ለማሳሳት የሚፈበረኩ መረጃዎችም እንደሚኖሩ መረዳት ይቻላል። ሁሉንም ደግሞ መቆጣጠርና መከላከል አዳጋች መሆኑ ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መሐመድ እድሪስ በበኩላቸው፣ የአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲጎለብት የሀሳብ ነፃነት ከፍተኛ ሚና እንዳለው ጠቁመዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሐሰተኛ መረጃና ጥላቻ ንግግር እየተስተዋለ እንደሚገኝና ለእዚህ ደግሞ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ምክክር እየተደረገበት መሆኑን ነው ያስታወቁት።

በኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለው የሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ስርጭት እየሰፋና በሕዝብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው። ይህም የመረጃ አካላት ትክክለኛውን መረጃ በወቅቱ ባለማድረስ እንደሚፈጠርና በሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ እንቅፋት እየሆነ መምጣቱን አንስተዋል።

ሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር የአገር ግንባታን ሊፈትን ስለሚችል ችግሩን ለመግታት የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችን ለኅብረተሰቡ ማስገንዘብ እንዲሁም ተጠያቂነትን ማስፈን ላይ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ የመፍትሔ ሀሳብ ያሉትን አቶ መሐመድ ጠቁመዋል።

ዶክተር ለገሰ ደግሞ፤ ሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግርን ለመታገል የመፍትሔ ሀሳብ በማለት የጠቀሱት በቅድሚያ የኅብረተሰቡን ንቃተ ሕሊና ማሳደግ ላይ መሥራት ነው ። ኅብረተሰቡ በሐሰተኛ ወሬዎች እንዳይወሰድ፣ እውነት እና ሐሰት የሆኑ ነገሮችን መለየት እንዲችል ግንዛቤውን ማሳደግ ዋነኛ ጉዳይ መሆን አለበት ብለዋል።

በመረጃ ተቀባይና በመረጃ አጋሪው ዘንድ ያለውን ክፍተት እንዴት እንሙላው በሚለው ዙሪያ ወይዘሪት ረሆቦት የመፍትሔ ሀሳብ ያሉትን አጋርተውናል። አንደኛ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ደረጃ ሐሰተኛውን መረጃ ከእውነታው እንዴት መለየት እንደሚችሉ እውቀቱ እንዲኖራቸው ማድረግ፤ ዋና ዋና የሚባሉ መደበኛ መገናኛ ብዙኃን ደግሞ ትክክለኛውን መረጃ በፍጥነት መስጠት እንዲሁም የመረጃ ማጣራት ተቋሞችን በማስፋፋት መረጃዎችን በፍጥነት አጣርቶ እውነታውን ለሕዝቡ ማሳወቅ ይገባል። አሁን ባለው ሁኔታ በሀገር ቤት ሁለት ሀገር በቀል የመረጃ ማጣራት ሥራ የሚሠሩ ተቋማት ብቻ ናቸው ያሉት። በመሆኑን ሁሉንም ሐሰተኛ መረጃዎች አጣርቶ እውነታውን ማሳወቅ አይቻልም ብለዋል።

ሁሉም አስተያየት ሰጪዎች የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ ሕዝብንና ሀገርን እየጎዳ መሆኑን፤ በሚሰራጩ ሐሰተኛ መረጃዎች ምክንያት በሀገራችን እጅግ አስከፊና አሳዛኝ ጭካኔ የተሞላባቸው ጥቃቶች ሃይማኖትንና ማንነትን መሠረት አድርገው መፈጸሙን ተስማምተውበታል። በመሆኑም ይሄ ጥፋት አሁን ካለው በላይ ተስፋፍቶ እንዳይቀጥል ሕዝቡ ሐሰተኛ መረጃዎችንና የጥላቻ ንግግሮችን መለየት እንዲችል ከስር ጀምሮ ማስተማር፣ ንቃተ ሕሊናውን ማሳደግ እንዲሁም ሕዝብን ከሕዝብ፤ ሃይማኖት ከሃይማኖት ለማጋጨት በሚሠሩት ላይ ደግሞ በሕጉ መሠረት እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

ባለሙያዎቹ የሰጡት ሀሳብ በፍጥነት የማይከናወን ከሆነ ግን አሁን ከሚታየውና ከሚሰማውም በላይ የሀገርን አንድነት እና የሕዝቦች ማኅበራዊ መስተጋብር ፈተና ውስጥ የሚከት ይሆናል። ሀገርም ለብተና ይዳርጋል።

**የኅብረተሰቡን የአኗኗር ባህል የሚሸረሽር የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃዎች በተለያየ መንገድ ይተላለፋል። ይሄ በተለይ በአሁኑ ወቅት ትልቅ ፈተና ሆኗል። ሐሰተኛ መረጃዎች በተለይ በስፋት የሚሰራጩት በዩቲዩውብ፣ በቲውተር፣ በቴሌግራም እና በኢንስታግራም ነው። በሌሎች እንደ ቲክ ቶክ ባሉት የመገናኛ ዘዴዎች ይተላለፋል። በመሆኑም ኅብረተሰቡ ይህን መረዳት አለበት። የሚያገኛቸውን መረጃዎችም ለራሱም ሆነ ለሌሎች ከማሰራጨቱ በፊት እውነታውን ማወቅ አለበት**

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የኢትዮጵያ ሴት ጋዜጠኞች ባለውለታ

**ሰላማዊት ውቤ**

የኢትዮጵያ ሴት ጋዜጠኞች ማህበርን ከመሰረቱት ሴት ጋዜጠኞች አንዷ ነች። ለጋዘጠኝነት ሙያዋ ከሴቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊነቷ እስከ መነሳት ተሰውታለታለች። ሙያውን በክፉ ወቅቶች ሳትሸሽው ለዛሬ ያበቃችው በመሆኗ ከሌሎቹ ትለያለች ተካበች አሰፋ። በቅርቡም የሴት ጋዜጠኞች ማህበር ለውለታዋ ዕውቅናና ምስጋና የቸራት ተካበች የተወለደችው አዲስ አበባ ከተማ ካዛንቺስ አካባቢ በ1939 ዓ.ም ነው።

ለወላጆቿ ከ11 ልጆች መካከል ሦስተኛ ልጃቸው ነች። በተለይ ለስድስቱ እህቶቿ እንደወንድምም ሆና ነው የኖረችው። ሊተነኩሳቸው የከጀለ ሁሉ ጋሻና መከታቸው ናት።

ለመምህራኖቿና ለአለቆቿ በአጠቃላይ ለሰው ልጆች ክብር ትሰጣለች። ሆኖም የማትፈራ ደፋርም ነች። ባላመነችበት ጉዳይ እስኪታሳምን መከራከር ትወዳለች። እግር ኳስ ባትጫወትም ጨዋታ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ሁሉ ተገኝታ ትመለከታለች። በስፖርት የተገነባው ቁመቷ መካከለኛ፤ የፊቷ ቀለም ብስል ቀይ፤ ገጽታው ስልክክ ያለ ሳቢና ማራኪ ቢሆንም የተቆጣ የሚመስለው ንግግሯ ከአካሄዷና ሱሪና ኮት አለባበሷ ጋር ተዳምሮ ወንዳወንድ ያስመስላታል።

ከሰው ባትጣላም በዚህ ሁኔታዋ እንኳን ሴቶቹ ወንዶቹም ሲፈሩና ሲያከብሯት፤ እሷም ስትመካበትና የደፈራትን ሁሉ አፈር ድሜ እያስጋጠች አሸናፊነት ስትጎናፀፍበት ኖራለች። ሁሌም አሸናፊ ነች። እህቶቿን ከለከፉ የትኞቹንም ወንዶች ሳትደበድብ አትለቅም። ዱላዋን የቀመሰ ጎረምሳ ሁለተኛ ቀና ብሎ እንኳን አያያቸውም። የማያውቅ ሊነካቸው ከሞከር ‹‹አንተ የዛች የእንትና እህት እኮነች ዋ! ይባባላሉ። ወንድሜን ሲያገኙት ያቺ እህትህ ደህና ነች አቤት እንትናን እኮ እንዴት አድርጋ እንደደበደበችው ይሉታል። ድብድቡን የተወችው ዕድሜዋ 20ዎቹን አልፎ ወደ 30ዎቹ ሲንደረደር ነው። ትምህርት ጨርሳ ሥራ ይዛለች። ወቅቱ ደርግ የመጣበት በመሆኑ ሁኔታውን ለማየት ወደ አራት ኪሎ ስትሄድ አንዱ ተከሻዋን ይመታታል።

ሆኖም በዕድሜዋም በስላ ፤ ትምህርቷን አጠናቃ ሥራ ይዛለችና የሰውየውን ድርጊት አይታ እንዳላየ አለፈችው። ‹‹ዞር ብዬ አይቼው ዱሮ ቢሆን ይሄኔ እንኳን ነክቶኝ ቢናገረኝ እንደማለቀው እያሰብኩ ሳቅኩና ሄድኩ›› ትላለች።

ለእሷ ባይመስላትም ንግግርዋ ጠንከር ያለ የወንዳወንድ በመሆኑ አንዳንዶች ለምን ትቆጭያለሽ ይሏታል። ሆኖም ጨዋታ አዋቂ፣ ሩህሩህ ፣ቀልደኛና የዋህም ነች። ውስጧን ሳያዩ ሲፈሯት የቆዩ ሰዎች ይሄን ባህሪዋን የሚያውቁት ሲግባቧት ነው።

የጋዜጠኝነትን ስራ ሀሁ ብላ ለጀመረችበት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጥሩ አመለካከት አላት፡፡ ትወደዋለች፡፡ ‹‹የሚያካሂዳቸውን ግንባታዎችና የሥራ እንቅስቃሴውን ሳልፍ ሳገድም ሳየው ደስ ይለኛል›› ትላለች፡፡የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተማሪዬ፣ መመኪያና የዓይኔ ብሌን ስትልም ታሞካሸዋለች። ከድሮ ጀምሮ ፕሬስ ውስጥ ሰላም ነበር። የተሻለ መተሳሰብና መቀራረብም ይታያል። ሌሎች ሚዲያዎች እርስ በእርስ የሚናቆሩበት ነበር። ማህበራዊ ሕይወታቸውም የላላ ነው። ፕሬስ ሥራውም ቢሆን አርአያነት ያለው፤ ዘመን ተሻጋሪና ታሪካዊ አሻራ የሚያሳርፍ ነው ትላለች። 44 ዓመታት ከሚጠጋው የሥራ ዘመኗ ከ30 በላዩን በዚሁ ድርጅትና በኢትዮጵያ ሴት ጋዜጠኞች ማህበር በጋዜጠኝነትና በአመራር ሙያ በማገልገል ነው ያሳለፈችው።

የተማሪዎች ረብሻ ደስታ ስለሚነሳት መምህር መሆንን አትፈልግም ነበር፡፡ ሆኖም እየማለችና እየተገዘተች ትጠላው በነበረው በመምህርነት ሙያ ተሰማራች። ቀድሞ በየነ መርድ አሁን ዕድገት በሕብረት በተሰኘው ትምህርት ቤት ለ13 ዓመታት የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን በፍቅር አስተምራለች ።ተማሪዎቿ በልጅነቷ እንደፈራችው ባህርያቸው የሚያውክ አልነበረም። ይወዷትና ያከብሯት እንደነበረም ታወሳለች። ለውጤታማነቷ በመምህርነት ሥራ ጀምረው እስከ ትምህርት ሚኒስቴር በኃላፊነት ያገለገሉት አባቷ ልምድ መቅሰሚ ረድቷታል።

አባቷ በልጅ አስተዳደግ ላይ ቀልድ አያውቁም። ሁልጊዜ ማታ ማታ በየተራ ደብተራቸውን መፈተሻቸውና የፈተና ወረቀት ማየታቸው ግድ ነበር። እሷና እህቶቿ አንድ ኤክስ ከተገኘባቸው እንዴት ሆኖ ገባ ፤ ለምን



አንጋፋዋ ጋዜጠኛ ተካበች አሰፋ

አስተማሪያችሁን አልጠየቃችሁም ይባላሉ። ኮርኮም መደረጋቸውም አይቀርም። እናታቸውም እንዲሁ የልጆቻቸው ትኩረት ትምህርታቸው ላይ እንዲሆን ይፈልጋሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ካዛንቺሽ በሚገኘው በቀድሞው አስፋወሰን በአሁኑ ምስራቅ ጎህ ፤የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ በቀድሞው ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በአሁኑ ኮከበ ጽባህ ት/ቤት ያጠናቀቀችው በዚህ መልኩ ነው። በ13ቱ ዓመት ቆይታዋ ተማሪዎቿን እንደዚሁ ስትቀርጽም ኖራለች። የጋዜጠኝነቱን ትምህርት ቀስማ በሙያው ለመሰማራት የበቃችውም የመምህራን ማህበር የአዲስ አበባ ከተማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ገንዘብ ያዥ በነበረችበት ሰዓት ባገኘችው የነፃ ትምህርት ዕድል ነው።

በ1976 ዓ.ም በውድድሩ አሸንፋ ወደ ችኮዝላባኪያ በማቅናት ለአምስት ዓመታት የጋዜጠኝነት ትምህርት ተምራ የማስተር ኦፍ አርት ሁለተኛ ዲግሪዋን ይዛ ተመልሳለች። ፈጥናም ለማስታወቂያ ሚኒስቴር አመለከተችና 1983 ጥቅምት አንድ ቀን ፕሬስ ድርጅት ተመደበች፡፡ የጋዜጠኝነት ሥራንም አሀዱ አለች። ድርጅቱ በሚያሳትማቸው በአዲስ ዘመን ጋዜጣና በየካቲት መጽሔት እስከ 1986 ዓ.ም ስትሰራ ቆየች። በየመሥሪያ ቤቱ የሴቶች መምሪያ ይቋቋም ሲባል ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር በዚሁ በ1986 አጋማሽ ተዛወረች።

ተካበች አሁን ላይ አሜሪካ ከምትኖረው ከፍፁም አለማየሁ ፣ ከአባይነሽ ብሩ ከቅድስት ክፍለዮሐንስና ከሌሎች ጋዜጠኞች ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ሴት ጋዜጠኞች ማህበርን የመመስረቱ ሃሳብ የመነጨላትም ይሄኔ ነው። ይግባቡና ይቀራረቡ ከነበሩትና ተመሳሳይ ሃሳብ ከነበራቸው ባልደረቦቿ ፍፁም አለማየሁ አባይነሽ ብሩ ፣ ስርጉት አስፋው፣ ኢሌኒ መኩሪያ፣ ከአሜሪካ ኤምባሲዎቹ ወይዘሮ አለምሰገድና ወይዘሮ ታቦቱን ጨምሮ ከፋና ሬድዮዋ ቅድስት ክፍለዮሐንስ፣ ከፕሬሷ ኤልሳቤጥ እንድሪያስ፣ ከፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ ደራሲና ጋዜጠኛ የምወድሽ በቀለና ከሌሎች ሴት ጋዜጠኞች ጋር እየተገናኘች ሃሳቡን ስታብላላ ቆየች።

በዚሁ ወቅትም ዓለም አቀፍ የሴቶች ጉባኤ በየአህጉሩ ሲደረግ አፍሪካ ሴኔጋል ዳካር በተካሄደው ተሳተፈች። ከዚህ መልስም ዓለም አቀፍ ጉባኤ በቤጂንግ ቻይና ተካሄደ። እዚህ ደግሞ በወቅቱ የሴቶች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ ወይዘሮ ታደለች ኃይለሚካኤል ተካፈለች። ከቤጂንጉ ጉባኤ 12 ዋና ዋና ነጥቦች አንዱና ዋናው ሴቶችና ሚዲያ የሚል ነበርና እነተካበች በስብሰባው የተሳተፈችውን ወይዘሮ ታደለችን በየሚዲያው ለሚሰሩት ሴቶች እንድታስረዳ ስብሰባ አዘጋጅተው ጋበዟት። ሴት ጋዜጠኞቹ የራሳችን ማህበር እንመስርት የሚል ሃሳብም አነሱ።

ሆኖም ስብሰባው የግማሽ ቀን በመሆኑና ሰዓት በመድረሱ ሃሳቡ መቋጫ ሳያገኝ መድረኩ ተበተነ። አንዳንድ ሴት ጋዜጠኞች ሃሳቡን ለአለቆቻቸው በመንገራቸው የምስረታ ውጥኑ በስፋት እየተሰማ መጣ። በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩት ጆሮም ገባ። በትላልቆቹ አለቆች ዘንድ የኢትዮጵያ ጋዜጠኖች ማህበር እያለ ለብቻው ሌላ ማህበር መመሥረት ለምን

**አንዳንድ ሴት ጋዜጠኞች ሃሳቡን ለአለቆቻቸው በመንገራቸው የምስረታ ውጥኑ በስፋት እየተሰማ መጣ። በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩት ጆሮም ገባ። በትላልቆቹ አለቆች ዘንድ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር እያለ ለብቻው ሌላ ማህበር መመሥረት ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄና ቅሬታም አስነሳ። እነተካበች ለዚህ በየሚዲያ ተቋማቱ ለተነሳ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ምክክር አደረጉ**

አስፈለገ? የሚል ጥያቄና ቅሬታም አስነሳ። እነተካበች ለዚህ በየሚዲያ ተቋማቱ ለተነሳ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ምክክር አደረጉ።

የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር ቢኖርም ለሴት ጋዜጠኞች ሰፊ ዕድል የሚሰጥ አለመሆኑን አስረዱ። በተለይ በወቅቱ ሴት ጋዜጠኞች አገር ውስጥ በሚሰጡ አጫጭር የጋዜጠኝነት ስልጠናዎች እንደወንዶች ቀርቶ በጥቂቱ እንኳን እየተሳተፉ እንዳልሆነም ተናገሩ። በዚህ የተነሳ በመገናኛ ብዙሃኑ ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎ ውሱን ሆኖ ለመቆየት መገደዱንም አነሱ። በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ ራሱን ችሎ የጋዜጠኝነት የሚሰጥ ተቋም ባለመኖሩ ማኅበሩ መቋቋሙ ሴት ጋዜጠኞች ለመብታቸውና ለጥቅማቸው እንዲታገሉ ከማድረጉ ባሻገር በርካታ ሴቶችን በአገር ውስጥና በውጪ በሚሰጡ አጫጭር የጋዜጠኝነት ሙያ ኮርሶች በማሰልጠን በስፋት ሴት ጋዜጠኞችን ማፍራት እንደሚያስችልም ጠቀሱ። ማህበሩን በዋንኛነት መመስረት የፈለጉት ለዚህ መሆኑንም አፍረጠረጡት።

ሆኖም ምላሹ በስርዓቱ አቀንቃኞች በበጎ ዓይን አልታየላቻም። እንደ አሳዳሚ ተቆጥሮባቸው እነተካበችን ካድሬ ጥርስ ውስጥ አስገባቸው። ይባስ ተብሎ በዓመት አንዴ በሚከበር የመገናኛ ብዙሃን በዓል ላይ ዕውቋ የሬዴዎዋ ጋዜጠኛ አባይነሽ ብሩ ሴቶችና ሚዲያ የሚል ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅታ አቀረበች። በጽሑፏ በሚዲያው ላይ ብዙ ሴቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዳልሆኑ ፤ያሉትም በበርካታ ተፅዕኖዎችና ችግሮች ላይ መሆናቸውንም አመላከተች። ችግሩን ለመፍታት ማህበሩ መመስረት መፍትሄ እንደሚሆንም በውይይቱ ጎልቶ ወጣ። ይሄ የአመራሮቹን ቅሬታ አባባሰው። አባይነሽ አመራሮች ፊት ማህበሩ መመስረቱ እንደማይቀር መናገሯም በጥሩ አልተወሰደም።

በዚህ ወቅት ማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር አንድ መሥሪያ ቤት ሆኖ ተቋቋመ። ይሄው ሰበብ ሆነና በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ የነበረው የሴቶች ጉዳይ መምሪያ በ1988 ዓ.ም ፈረሰ። ተካበችም ከሴቶች መምሪያ ኃላፊነቷ ተነሳች። ወደመጣችበት ወደ ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ተመለሰች። አብረዋት ይሰሩ የነበሩትም ሁለት ባለሙያዎች ወደየመጡበት የሚዲያ ተቋም ተመለሱ። በወቅቱ የነበሩት የፕሬስ አለቆቿ ፊት አልነሷትም። አንዳንድ የዘመኑ ካድሬዎች ከደረጃዋ ዝቅ ብላ እንድትሰራ ምኞት ቢኖራቸውም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ኃላፊዎች ተሟግተው የድርጅቱን የዜና ማዕከል በዋናነት እንድታስተባብር አደረጓት።

የፎቶግራፍ ባለሙያ ከመመደብ ጀምሮ ጋዜጠኞችን በማሰማራት ለማኔጅመንቱ አባላት ኤዲቶሪያል ላይ የዕየለቱን አፈፃፀም በማቅረብ ከድርጅቱ ኃላፊዎችና ከላይ እስከታች ካለው ሰራተኛ ጋር ተግባብታና ተመካክራ ስታገለግል ለዓመታት ቆየች። ወቅቱን ባታስታውሰውም ወደ አዲስ ዘመን አምዶች ዝግጅት ክፍልም ተዛውራ ስትሰራ ቆይታለች። ዛሬ ላይ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚ ፣ ፖለቲካና ሕግ ተብሎ በመከፋፈል እየተሰራበት ያለው ልምድ ከዚሁ መመዘዙንና እየጎለበተ መምጣቱን ታወሳለች። ምን እንጠይቅሎት የሚሉና በርካታ የሕክምና፣ የሕግና ሌሎች የውጪ ባለሙያዎች ከየሙያቸው አንፃር ሰፊ ትምህርታዊና አዝናኝ ማብራሪያ የሚሰጡባቸውም አዳዲስ ዓምዶች ላይ የመስራት ዕድሉን አግኝታ ጡረታ እስከ ወጣችበት 2003 ዓ.ም መጨረሻ አገልግላለች።

አንጋፋዋ ጋዜጠኛ በዚህ ሁሉ መካከል የኢትዮጵያ ሴት ጋዜጠኞች ማህበር መመስረት ውጥኗን አልዘነጋችም። በራሳቸው ወጪ ሻይ ቡና እያዘጋጁ በሚያደርጉት ውይይት ትገኝ ነበር።

እንዳወጋችን በሥራ ጫና እሷ ባትገኝም በተለይ የኒዘርላንድ ኤምባሲ አንደኛ ፀሐፊ የሆነው ሚስተር ቦካንሰን ለምስረታው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ቦካንሰን በራሱ ወጪና በራሱ ቤት የራት ግብዣና ሻይ ቡና እያዘጋጀ የተወሰኑ ሴት ጋዜጠኞችን በማሰባሰብ ስለ ማህበሩ ምስረታ ሲያወያይ ቆይቷል። ብዙ መስዋዕትነት የተከፈለበት የኢትዮጵያ መገናኛ ባለሙያዎች ሴት ማህበር (ኢትመባሴማ ) በ1991 ዓ.ም በታህሳስ ወር ተመሰረተ። በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የእንግሊዝኛው ክፍል ባልደረባ ፍፁም አለማየሁም በፕሬዚዳንትነት ፣ ተካበች አሰፋ በገንዘብ ያዥነት ተመረጡ። እስከ ፕሬዚዳንትነትና ሥራ አስፈፃሚነት ደጋግማ በመመረጥ አገልግላለች።

ከምስረታው በኋላ በስፋት ድጋፍ ይገኝና ስልጠና ይሰጥ ስለነበረ ጥሩ እንቅስቃሴ ነበር ማለት ይቻላል። በተለይ ምንም ዓይነት የጋዜጠኝነት ስልጠና ባልነበረበት ወቅት ፍሬደሪክ ኤቨርት የተሰኘው የጀርመን ድርጅት በርካታ አጫጭር ስልጠናዎችን ሲሰጥ ቆይቷል። የኢትዮጵያ ማስ ሚዲያ ኢንስቲትዩትም የተቋቋመው ከዚህ በኋላ በመሆኑ አበርክቶው ቀላል አልነበረም። ከዚሁ ጎን ለጎንም ማህበሩ በተለይ ኢንስቲትዩቱ ገብተው የመማር ዕድል ላላገኙ አባላቱና ሴት ጋዜጠኞች በየመገናኛ ብዙሃን ዘርፉ የውጭና የአገር ውስጥ አጫጭርና ረጃጅም ሙያዊ ስልጠናዎችን ሲሰጥ ቆይቷል። ብዙዎቹ በዘርፉ የራሳቸው የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የተሻለ ደረጃ ለመድረስ በቅተዋል።

1997 ዓ.ም ሞቅ ደመቅ ያለው የኢትዮጵያ መገናኛ ባለሙያዎች ሴት ማህበር (ኢትመባሴማ ) እንቅስቃሴ እየተቀዛቀዘ መጣ። ምክንያቱ በወቅቱ ስልጣን ላይ የነበረው ኢህአዴግ ከፍተኛ ሽንፈት ስለደረሰበት ያወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የሚያስር አዲስ አዋጅ ነበር። አዋጁ ሁለት መልኮች ሲኖሩት አንዱ በማህበሩ አባላት ላይ ብቻ የሚሰራ ከሆነ ከውጪ አገር 90 በመቶውን 10 በመቶውን ደግሞ ከአገር ውስጥ ማግኘት እንደሚችል ይደነግጋል። ለሶስተኛ ሰው የሚሰራ ከሆነ 90 በመቶውን ከአገር ውስጥ 10 በመቶውን ድጋፍ ከውጪ እንደሚያገኝም ያስቀምጣል። ከፍተኛ ገንዘብ የነበራቸውንና ለማህበሩ ድጋፍ ያደርጉ የነበሩትን ገንዘባቸውን ሁሉ ወረሰ። ለአብነት የኢኮኖሚ ባለሙያዎችና የነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ሰብዓዊ መብት ድርጅት ይጠቀሳል።

የውጪ ድርጅቶችም ቢሆኑ ከመንግስት ጋር መጋጨት አይፈልጉምና ሸሹ። የማህበሩ እንቅስቃሴ እጅግ ተቀዛቀዘ። ከ16 በላይ ሰራተኞቹ ውስጥ አብዛኞቹ ደመወዝ ሊከፍላቸው ባለመቻሉ ተበተኑ። በተለይ ጡረታ ወጥታ ሙሉ ጊዜዋን ለማህበሩ ባደረገችበት 2005 ዓ.ም የነበሩት ፀሐፊ፣ ሂሳብና ጽዳት ሰራተኞች ገቢው ሲነጥፍ ለቀቁ። ብዙ መስዋዕትነት ከፍላ ለምስረታ ያበቃችው የክፉ ቀን ወዳጁ ተካበች አሰፋ ብቻ ቀረች። ቢሮው እንዳይዘጋ፤ የማህበሩ ስም እንዳይዘነጋ፤ አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን እያደረገች ባዶ ቤት መዋል ጀመረች።

ረጃጅም መንገዶችን በእግር በመጓዝ፤ በልመና ፊት በመገረፍ ለዓመታት ገንዘቧንና ጊዜዋን እየሰዋች ህልውናውን አሰነበተችው። የኢትዮጵያ መገናኛ ባለሙያዎች ሴት ማህበር (ኢትመባሴማ) አሁን ላይ በተካበች ጥረት ውዝፍ የቤት ኪራዩን ዘግቷል። ቢሮውን አዘምኖና የራሱ ስቱዲዮ ገንብቷል። ጠቅላላ ጉባኤ ጠርቶ አዲስ የቦርድ አመራሮችንም መርጦ ወደ ሥራ ገብቷል። ተካበች በዚህ ውስጥ የቀድሞ ሥራ አስፈፃሚ አባል የሶሎሜ ደስታ አስተዋፅኦ ጎልቶ መውጣቱን በመግለፅ ሃሳቧን አሳርጋለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

**በ1957 ዓም የታተሙትን የአዲስ ዘመን ጋዜጦች መለስ ብለን በመቃኘት ከግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት የነበሩ ዘገባዎችን ተመልክተን ለዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ አምዳችን በመቀጭንጨብ አቅርበናቸዋል። በወቅቱ አሁን ከጀመርነው ክረምት ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ዛፎች ለመትከል ከሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩ ዘገባዎችን ተመልክተናል። በባሌ በርካታ ችግኞች እንደሚተከሉ የሚነግረን ዝርዝር ዘገባ፣ የሚተከሉትን የችግኝ ዓይነቶች ብዛት ይገልፃል። እንዲሁም ተማሪዎች ክረምቱን በእንዝላልነት እንዳያሳልፉ በአዲስ አበባ በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች መማር ለሚፈልጉ ማጠናከሪያ ትምህርት ለመስጠት መታሰቡንና ሌሎች ዘገባዎች መርጠን እንድታነቡት እነሆ ብለናል።**

### ለባሌ ዛፍ ተካዮች ፬፻፳ ሺህ ችግኞች

የባሌ ጠቅላይ ግዛት የእርሻ ሚኒስቴር ተጠሪ ፬፻፳ ሺህ የዛፍ ችግኞች ማዘጋጀቱን ኢ-ወ-ም ገልጧል፤ ችግኞቹ በቅርብ ጊዜ ለተካዮች ይታደላሉ።

ለመታደል የተዘጋጁት ችግኞች ፪፻፶ ሺህ የባህር ዛፍ ፩፻፶ ሺህ የውጭ አገር ግራር ፴ሺህ የውጭ አገር ጥድ ፴ሺህ ያገር ውስጥ ጥድ ፲ ሺህ ዝግባ ናቸው።

ከነዚህም በቀር የጓሮ አትክልት ችግኞች የተዘጋጁ በመሆናቸው እነዚህ ችግኞች ለገበሬዎች እንደሚታደሉ የጠቅላይ ግዛቱ የእርሻ ሚኒስቴር ሥራ አስኪያጅ አቶ ኃይለ ገብርኤል ሀብተማርያም ገልጠዋል።

(ሰኔ 20 ቀን 1957 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)

### ተማሪዎች እንዳይማግጡ የክረምት ትምህርት ቤት ይከፈታል

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ በሚመጡት የክረምት ወራት ማለት ከሐምሌ ፩ ቀን እስከ ጳጉሜ ፫ ቀን ፶፯ ዓ/ም/ በአዲስ አበባ በሚገኙት ልዩ ልዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለወጣቶች ለሌሎችም መማር ለሚፈልጉ ሁሉ ትምህርት ይሰጣል። የትምህርቱም ደረጃ ከአንደኛ ክፍል እስከ ስምንተኛ ክፍል ሲሆን ትምህርቱንም የሚሰጡት የዩኒቨርስቲ ትምህርት ያላቸው አስተማሪዎች መሆናቸው ታውቋል።

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ ወጣቶች በክረምት ወራት ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በጠቃሚ ትምህርት ላይ እንዲያውሉት ማድረግ ነው። ተማሪዎቹ በልዩ ልዩ ምክንያት ሳይማሩ የቀረባቸውንም ትምህርት በክረምቱ ወራት ለመማር እንዲችሉ፤ደካማ የሆኑበትንም ትምህርት በጠለቀ መንገድ እንዲያሻሽሉ፤ በአሰልቺዎቹ የክረምት ወራት ያለምንም ሥራ ከቤት ውለው ዘመዶቻቸውን ከማስቸገርና ዘወትር በተጠሉና በማይፈለጉ ሥራዎች በመዋል መጥፎ ጠባይና ዓመልን ከመቅሰም እንዲታቀቡ ለማድረግ ዩኒቨርስቲው ያቀደው ፕሮግራም ዓይነተኛ መፍትሔ መሆኑ አይጠረጠርም።

ትምህርት ለጊዜው በአምሐ ደስታ፣ በዳግማዊ ምኒሊክ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተመላላሽ በአስፋው ወሰን፣ በሽመልስ ሀብቴ፣ በወይዘሮ ቀለመወርቅ፣ በልዑል መኰንንና በመድኃኒዓለም ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይሰጣል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሌሎች ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ የሚከፈቱ መሆናቸው ይታመናል። ትምህርት ቤቶቹ የሚሰጡዋቸው የትምህርት ዓይነቶች አማርኛ፣ ሂሳብ፣ እንግሊዝኛ፣ ኅብረ ትምህርትና (ሶሺያል ስተዲስ) ሥነ ፍጥረት ናቸው።

የትምህርት ቤቶቹ ጠቅላላ አመራርና የትምህርት አሰጣጥ በዩኒቨርስቲውና በትምህርት ሚኒስቴር የቅርብ ተቆጣጣሪነት ሥር እንደሚሆን ታውቋል።

በነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተመዝግበው ትምህርት ለመቀጠል የሚሹ ሁሉ በየወሩ ፬ (አራት ብር) መክፈል ይኖርባቸዋል። በዚህ ዓይነት የተገኘው ገቢ ትምህርት ቤቶቹን ለማካሄድ በቂ ሆኖ ካልተገኘ የሚቀረውን ዩኒቨርስቲውና የትምህርት ሚኒስቴር ለመክፈል ቃል መግባታቸውን የዩኒቨርስቲው የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት የወጣው መግለጫ አስገንዝቧል።

የትምህርት ሚኒስቴር ለመማሪያ የሚያገለግሉ መጻሕፍትን ለዩኒቨርስቲው ለመስጠት ተስማምቷል። ዩኒቨርስቲውም ትምህርቱን የሚያቀርበው ሚኒስቴሩ ባወጡት ካሪኩለም መሠረት እንደሚሆን ታውቋል።

(ሰኔ 19 ቀን 1957 የወጣው አዲስ ዘመን)

### ፭ የውጭ ሀገር በጎች በ፭ሺ ብር ተገዝተው መጡ

አምስት በጎች በአምስት ሺህ ብር ከፈረንሳይ ሀገር ተገዝተው ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል ፤በጎቹ የተገዙት በባሌ ግዛት ለተቋቋመው የበግ ርባታ ሥራ ነው። እነዚህ ከፈረንሳይ ሀገር የተገዙት አምስት በጎች በዓለም የታወቁት የበግ ዘሮች ውስጥ ምርጥ የሆኑት ናቸው።

እነዚህ በጎች በሀገራችን ካሉት በጎች ጋር ተደባልቀው ዘራቸው በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲባዛ ታስቦ የተገዙ ናቸው፤ለሱፍ ጠጉር ሥራ የሀገራችን በጎች ከውጭዎች ጋር በማዳቀል ጥሩ ጠጉራም በጎችን ለማግኘት በቅርብ ግዜ ምርጥ የሆኑ በጎች ከኬንያ ተገዝተው በባሌ ጠቅላይ ግዛት ለተቋቋመው የበግ ርባታ ሥራ እንደሚደርሱ ታውቋል።

የበጎቹ ርባታ ሥራ አስኪያጅ ሚስተር ዋርት በባሌ ጠቅላይ ግዛት የተጀመረው የበግ ርባታ ሥራ በሚገባና ተስፋ ባለው ሁናቴ እንደሚካሄድ ገልጠዋል፤ለርባታው ሥራ አሥር ሺህ ያገር ውስጥ በጎች በተጨማሪ ለመግዛት ማስፈለጉንም ሚስተር ዋርት ተናግረዋል።

(ግንቦት 26 ቀን 1957 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)

### ሰውየው አንበሳውን በንክሻ አሸነፈ

ሉሲዮና ጃኦኮም ቻንሳ የተባሉ ወንድማማቾች በአንጎላ ውስጥ በሚያድኑበት ወቅት አንድ አንበሳ ሉሲያን ይዞ እመሬት ላይ ጥሎት ነበር።

ሉሲያም በአንበሳው በተያዘ ጊዜ በእጁ ጠብመንጃ ባለመያዙ አንበሳውን ለመከላከል አልቻለም። ግን ወንድሙ ደርሶ አንበሳው ጀርባ ላይ በመሆን አንበሳውን ከወንድሙ ለማላቀቅ ሞከሮ ሳይሆንለትም ቀረ።

በመጨረሻም ጃኢኪዮ ቻንሳ ወንድሙን ለማዳን ያደረገው ትግል ስላልተሳካት የአንበሳውን አፍንጫ ነከሰው፤በዚህ ግዜ አንበሳው የያዘውን ሉሲዮንን ስለለቀቀው፤ሊሲዮ ተነስቶ አንበሳውን በወንድሙ ጠብመንጃ ሊገድለው ችሏል።

ሁለቱ ወንድማማቾች ሰውነታቸው ስለተጫጫረ በሆስፒታል ውስጥ በመታከም ላይ ናቸው፤ ቁስላቸውም የማያሰጋ መሆኑንን ሮይተርስ አስረድቷል።

(ሰኔ 23 ቀን 1957 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)

# ዓለም አቀፍ

## በዴንማርክ ኮፐንሃገን ከተማ በገበያ ማዕከል ውስጥ በተከፈተ ተኩስ የሰዎች ሕይወት አለፈ




የዴንማርክ መዲና ኮፐንሃገን በሚገኝ አንድ የገበያ ማዕከል ውስጥ አንድ ግለሰብ በከፈተው ተኩስ ቢያንስ ሦስት ሰዎች ሲገደሉ ብዙዎች መቁሰላቸውን ፖሊስ አስታወቀ።ከቁስለኞቹ መካከልም ሦስቱ ከፉኛ የተጎዱ ናቸው ተብሏል።

በኮፐንሃገን ደቡባዊ ክፍል በሚገኘው ፊልድ የገበያ ማዕከል ውስጥ ይህንን ጥቃት የፈጸመው የ22 ዓመቱ ወጣት በቁጥጥር ሥር ውሎ ምርመራ እየተደረገበት መሆኑ ታውቋል። ፖሊስ ጥቃት ፈጻሚውን ያነሳሳው ምክንያት ምን እንደሆነ እስካሁን ግልጽ አይደለም ብሏል።

የዴንማርክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሜቴ ፍሬደሪክሰን “ዴንማርክ በጭካኔያዊ ጥቃት ተጎድታለች” በማለት ተጎጅዎችን በማጽናናት በእንደዚህ አይነት አስቸጋሪ ወቅት አንድ ላይ እንዲቆሙ ዴንማርካውያንን ጠይቀዋል።

“ውቧ እና በሰላሟ የምትታወቀው መዲናችን በሽርፍራፊ ሴኮንዶች ተመሰቃቅላለች” ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሯ። የዴንማርክ ዘውዳዊ ቤተሰብም የመጽናናት መልዕክቱን አስተላልፏል።

“ለደረሰው አስከፊ ነገር ምክንያቱን ባናውቅም ሰዎች ሕይወታቸውን ማጣታቸውና መቁሰላቸው ግን ግልጽ ሆኗል” ብሏል ከንጉሳዊው ቤተሰብ የወጣው መግለጫ።

ጥቃቱን በመፈጸም የተጠረጠረው ወጣት፣ ጠመንጃ እና ተተኳሾችን እንደያዘ በቁጥጥር ሥር መዋሉን ፖሊስ አስታውቋል። ተጠርጣሪው ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ፖሊስ ገልጿል።

ከጥቃቱ ጀርባ ሌሎች አቀናባሪዎች ስለመኖራቸው የተባለ ነገር ባይኖርም፣ የገበያ ማዕከሉ ውስጥ የሚገኙ ሱቆች ሁሉ ያሏቸውን የቪዲዮ ምስሎች ለማስረጃነት እንዲያቀርቡ ተጠይቀዋል።

ፊልድ የገበያ ማዕከል ከ140 በላይ ሱቆች እና ሬስቶራንት ያሉት ሲሆን ከመዲናዋ መውጫ አካባቢ የሚገኝ ነው።

የዐይን ምስክሮች እንደሚሉት የጥይት ተኩሱን ተከትሎ ገበያተኞች ከፍተኛ ግርግርና መደናገጥ ተፈጥሮባቸው ነበር።

ዴንማርክ በታሪኳ እንደነእዚህ አይነት ጥቃት ያስተናገደችው ከሰባት ዓመት በፊት በፈረንጆቹ 2015 ሲሆን፣ በጥቃቱም ሁለት ሰዎች የተገደሉ ሲሆን 6 ፖሊሶች ደግሞ ቆስለው ነበር። በወቅቱም ጥቃት አድራሹ በፖሊስ ተገድሏል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## የብሪታኒያ ሠራዊት የዩቲዩብና የትዊተር ገጾች መጠለፋቸው ተነገረ

የብሪታኒያ ሠራዊት የትዊተርና የዩቲዩብ አካውንቶቹ ባልታወቁ አካላት መጠለፋቸውን ተከትሎ ምርመራ እያካሄደ መሆኑ ተነገረ። የሠራዊቱ የዩቲዩብ መጠቀሚያ ከተጠለፈ በኋላ የዓለማችን ቢሊየነር ኤሎን መስክን ምስል የያዙ የክሪፕቶከረንሲ ቪዲዮዎች ታይተውበታል።

በተጠለፈው የትዊተር ገጹ ላይ ደግሞ ዲጂታል የጥበብ ሥራዎች መገበያያ የሆነው ኤንኤፍቲ በርካታ የትዊተር መልዕክቶች እንደገና ተጋርተውበታል።ሠራዊቱ የማኅበራዊ ሚዲያ ወደ ገጾቹ ባልታወቀ ወገን “ተሰብሮ እንደተገባ” አረጋግጦ፣ በመረጃ ደኅንነቱ ላይ “ጥብቅ ቁጥጥር” እንደሚያደርግ፣ ለተከሰተው ጠለፋ መፍትሔ ለመፈለግ እየሠራ መሆኑን ገልጿል።

በአሁን ወቅት ሁለቱም የዩቲዩብ እና የትዊተር አካውንቶች በሠራዊቱ በቁጥጥሩ ሥር መግባታቸው ታውቋል። የሠራዊቱ ቃል አቀባይ “የተከሰተውን



የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾችን ጠለፋ በተመለከተ አስፈላጊው ምርመራ እየተካሄደ በመሆኑ በዚህ ወቅት አስተያየት መስጠት ተገቢ አይደለም” ሲሉ ተናግረዋል።

እስካሁን የማኅበራዊ ገጾቹ ላይ ጠለፋውን የፈጸመው ወገን ማን እንደሆነ ያልታወቀ ሲሆን፣ የገጾቹ ስምም ተለውጦ ነበር።ገጹ ‘ባፔስክላን’ በሚል ስም ተቀይሮ የመለያው ምስልም ጦጣ በሚመስል የካርቱን ስዕል ተተክቶ ነበር።

እሁድ ዕለት ማታ የትዊተር አካውንቱ ከጠላፊዎቹ በማስለቀቅ በሠራዊቱ እጅ ስር መግባቱ ተነግሯል።ይህንንም ተከትሎ ሠራዊቱ "ገጻችን ላይ አጋጥሞ በነበረው ችግር ይቅርታ እንጠይቃለን። ምን እንደተከሰተ ለማወቅ ሙሉ ምርመራ የምናደርግ ሲሆን፣ ስለምትከተሉን እያመሰገንን ሙሉ አገልግሎታችን አሁን መልሶ ተጀምሯል" የሚል መልዕክት ሰፍሯል።

የብሪታኒያ ወግ አጥባቂ ፓርቲ የፓርላማ አባልና በምክር ቤቱ የመከላከያ ጉዳዮች ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት ተቢያስ ኤልውድ፣ የተከሰተው ነገር “አሳሳቢ ይመስላል” ሲሉ የሠራዊቱ የማኅበራዊ ገጾች መጠለፍ ቀላል ጉዳይ እንዳልሆነ አመልክተዋል። "ጠለፋውን በተመለከተ የሚደረገው ምርመራ እና የሚወሰደው እርምጃን በተመለከተ በተገቢው ሁኔታ እንደሚገለጽ ተስፋ አደርጋለሁ” ሲሉም የፓርላማ አባሉ በትዊተር ገጻቸው ላይ አስፍረዋል።

በትዊተር ላይ ከፍተኛ እውቅና ያላቸው ገጾች ሲጠለፉ ይህ የብሪታኒያ ሠራዊት ገጽ የመጀመሪያው አይደለም። ከሁለት ዓመት በፊት ዋነኛ የሚባሉ የአሜሪካ የትዊተር አካውንቶች በቢትኮይን አማካይነት ከሚደረግ ማጭበርበር ጋር በሚመሳሰል ሁኔታ ተጠልፈው እንደነበር ይታወሳል። ጠለፋ ከተፈጸመባቸው ገጾች መካከል የታዋቂዎቹ ኤሎን መስክ፣ ጄፍ ቤዞስ፣ ቢል ጌትስ፣ ባራክ ኦባማ፣ ጆ ባይደን እና የካኒዬ ዌስት እንደሚገኙባቸው የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## በዓለም ቻምፒዮና የሚሳተፈው ቡድን ጠንካራ ዝግጅት እያደረገ ነው

ብርሃን ፈይሳ

ይህ ወቅት የአትሌቲክስ ቤተሰቡ ዓይንና ልብ ወደ አንድ ስፍራ የሚያተኩርበት ነው፡፡ሃገራቸውን ማስጠራትና ብቃታቸውን ማስመስከር የሚፈልጉ አትሌቶች ህልማቸው የሚፈታበት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሊካሄድ 10ቀናት ብቻ ይቀሩታል፡፡ቻምፒዮናው በአሜሪካዋ ኦሪገን አዘጋጅነት ለ18ኛ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን፤ ከተማዋም ሆነች የውድድሩ ተሳታፊዎች ዝግጅታቸውን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ፡፡

በተለያዩ ርቀቶች አትሌቶቿን በውድድሩ ላይ የምታካፍለው ኢትዮጵያም ሶስት ሳምንታትን አስቀድማ የጀመረችውን ዝግጅት ወደማጠቃለሉ እየገባች ትገኛለች፡፡ከ800 ሜትር ጀምሮ በ1ሺ500 ሜትር፣ በ3ሺ ሜትር መሰናክል፣ በ5ሺ ሜትር፣ በ10ሺ ሜትር እንዲሁም በማራቶን በሁለቱም ጾታ የዓለም አትሌቲክስን መምረጫ መስፈርት የሚያሟሉ ከ43 ያላነሱ አትሌቶች ዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡13 አሰልጣኞች እንዲሁም 5 የህክምናና የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችም በቡድኑ ተካተው ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ዝግጅቱም በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ መም፣ በጂምናዚየም፣ በጫካ እንዲሁም ሌሎች ስፍራዎች ላይ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡የቡድኑ አባላትም በቻምፒዮናው ስኬትን አስመዝግበው የሃገራቸውን ስም ለማስጠራት ጠንካራ ዝግጅት በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡የ800 ሜትር አትሌቷና በዚህ ውድድር ሃገሯን የምትወክለው ሃብታም ዓለሙ፤ ዝግጅቱ በክረምት እየተደረገ ቢሆንም ያን ያህል አስቸጋሪ አለመሆኑን ትጠቁማለች፡፡ዝግጅቱ በመልካም ሁኔታ የቀጠለ ቢሆንም በውድድሩ ላይ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል በሚል ከወዲሁ እንደ ስጋት የሚነሳው ውድድሩ የሚካሄድበት አሜሪካ ለጉዞ ረጅም ርቀት መሆኑ ነው፡፡

አትሌት አብርሃም ስሜ በ3ሺ ሜትር መሰናክል ቡድን ውስጥ በተጠባባቂነት የተያዘ ሲሆን፤ ዝግጅቱ እንደ ሌላው ጊዜ ረጅም ባይሆንም በመልካም ሁኔታ እንደቀጠለ ይገልጻል፡፡ይህም በውድደሩ ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚረዳቸው ነው፡፡በዚህ ርቀት ኬንያዊያን አትሌቶች በተሻለ ስኬት የሚታወቁ ቢሆንም በቡድኑ ውስጥ ፈጣን ሰዓት ያላቸው አትሌቶች በመካተታቸው የውድድሩ የበላይነት በኢትዮጵያዊያን እጅ ይገባል የሚል ተስፋ እንዳለውም አትሌቱ ጠቁሟል፡፡

የቡድኑ አባላት በቀረው ጥቂት ጊዜ ለዓለም ቻምፒዮናው ስኬታማ ሊያደርግ የሚችል ዝግጅት በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ነው የሚገልጹት፡፡ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ውድድሮች በተለይ ዝናን ያተረፈችበት የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀት ብሄራዊ ቡድኑን በዋና አሰልጣኝነት እየመሩ ያሉት ኮማንደር ሁሴን ሽቦም ይንኑ ሃሳብ ይጋራሉ፡፡ለዚህ ውድድር በሃገር ውስጥ የተለያዩ ውድድሮችን ከማድረግ ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃም በዳይመንድ ሊጎች እና የማጣሪያ ውድድሮች ተሳታፊ በማድረግ በቂ ዝግጅት ሲያደርጉ መቆየታቸውን ያመላክታሉ፡፡ብሄራዊ ቡድኑ ተሰባስቦ ሰኔ 13/2014ዓም ሆቴል ከገባበት አንስቶ መልካም የሚባል ዝግጅት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡በስነልቦናም ሆነ በአካል ወቅታዊና ሳይንሳዊ ስልጠና ለአትሌቶች በመስጠት ቡድኑ ውጤታማ እንዲሆን እየተሰራ ነው፡፡

በኢትዮጵያ አሁን የክረምት ወቅት በመሆኑ ቡድኑ ዝግጅቱን የሚያደርገው ዝናብን ጠብቆ ነው፡፡ውድድሩ በሚካሄድበት አሜሪካ ደግሞ አሁን ሞቃታማ ወቅት ነው፡፡በመሆኑም ይህ የአየር ሁኔታ መለያየት እንዲሁም በኢትዮጵያ ቀን በአሜሪካ ደግሞ ማታ መሆኑ እንደ ስጋት ሊነሳ ቢችልም፤ ዝግጅቱ ግን ይህንኑ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ሌላው አትሌቶች በዳመንድ ሊግ እንዲሁም በሰዓት ማሚያ ውድድሩ ምክንያት በአጭር ጊዜ ውስጥ በተከታታይ በመሮጣቸው ኃይላቸውን በከፍተኛ ሁኔታ አውጥተው ተጠቅመዋል፡፡የማገገሚያ ጊዜም አለማግኘታቸውም እንደ ተጽእኖ ሊነሳ የሚችል ነው፡፡በመሆኑም ወደነበሩበት በመመለስ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ውድድር ተኮር ስልጠና ላይ ማተኮራቸውንም አሰልጣኙ ያስረዳሉ፡፡


የብሄራዊ ቡድኑ አባላት የመም ዝግጅት በማድረግ ላይ፤

የአንድ አሰልጣኝ ብቃት አትሌቶችን ለውጤት ማብቃት ብቻም ሳይሆን ጤንነታቸውን ጠብቆ መቆየትም ነው፡፡በመሆኑም እርሳቸው በሚያሰለጥኑት ርቀት የሚገኙ አትሌቶች በሙሉ ጤንነት ትኩረታቸውን በዝግጅታቸው ላይ አድርገዋል፡፡በመሆኑም እንደተለመደው ጥሩ ውጤት ይመዘገባል የሚል ተስፋ እንዳላቸው ነው አሰልጣኙ የሚገልጹት፡፡

Ethiopian Cooperative Commission (ECC)

ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

## የትምህርት ቤት ምገባና የአርሶ አደሮች የገበያ ትስስር

በዳንኤል አበበ

በአዲስ አበባ ከተማ በየዓመቱ ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ በከተማ አስተዳደሩ ተበጅቶለት ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን የዘለቀው የትምህርት ቤቶች ምገባ ፕሮግራም በርካታ ትሩፋት አስገኝቷል፡፡ፕሮግራሙ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት፣ የፖሊሲ ድጋፍ ያለው እና በዜጎቻችን ላይ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ኢንቨስትመንት ነው፡፡

የተያዘው የምገባ መርሃግብር እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡና ወደ ትምህርት ቤት የሚገቡ ልጆች ቁጥር እንዲጨምር ለማድረግ እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የመጡ ልጆች የምግብ ንጥረ ነገር እጥረት እንዳይገጥማቸው ጤናማና የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

በተጨማሪም ፕሮጀክቱ አርሶ አደሮች፣ ምግብ አዘጋጆችና አቀራቢዎች፣ ግብዓት አጓጓዦችን ጨምሮ በአካባቢው ለሚገኙ በሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች የስራ ዕድል በሚጠበቀው ልክ ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡በሂደትም ይህ ፕሮጀክት በከተማው የሚስተዋለውን የምግብ ዋጋ ግሽበት በመቀነስ ረገድ በእጅጉ አስተዋጽኦ እንደሚያመጣም ትልቅ ትልም ተሰንቆበታል፡፡

በአዲስ አበባ አስተዳደር ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንድ ሺ 69 ትምህርት ቤቶች ብቻ ወደ 628 ሺ ተማሪዎችን በምገባ መርሀ ግብሩ ተጠቃሚ እያደረጉ ይገኛል፡፡በዚህ የምገባ መርሀ ግብር ከ13 ሺ 400 በላይ የሚሆኑ እናቶች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡ የምግብ አዘጋጆቹ ተማሪዎችን በቀን ሁለት ጊዜ ቁርስና ምሳ እየመገቡ ይገኛሉ፡፡

ይሁን እንጂ ከግብርና ምርቶች ጋር ተያይዞ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራሙን የሚፈታተኑ ተግዳሮቶች ተጋርጠውበታል፡፡ከተግዳሮቶቹ መካከል ለትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራሙ የሚገዙ የግብርና ምርቶች ዋጋ በየጊዜው መናር፣ የምርቶች እጥረት፣ አርሶ አደሮቻችን ቀጥታ ተጠቃሚ አለመሆናቸው ብሎም መጋቢ እናቶች የሚያገኙት ገቢ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ ይጠቀሳል፡፡

ስለሆነም በአዲስ አበባ ከተማ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም እና በኦሮሚያ ልዩ ዞን አርሶ አደሮች መካከል ቋሚ እና ዘላቂ የግብርና ምርት የግብይት ትስስር መፍጠር ለነገ የሚባል የቤት ሥራ አይደለም፡፡እነዚህንና መሰል ችግሮችን በስርዓት (በሲስትም) ለመፍታት የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን እና የግብርና ሚኒስቴር በአዲስ አበባ ዙሪያ ከሚገኙ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ውስጥ ከተደራጁ አነስተኛ ማሳ አርሶ አደሮች ጋር በግብርና ውል ስምምነት (በሽጦ ማምረት መርህ) ዘላቂ እና አስተማማኝ ትስስር በመፍጠር ችግሩን በመሰረታዊነት ማቃለል ይቻላል በማለት ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማካተት አመርቂ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ናቸው፡፡

የዚህ ፕሮግራም ቀጣይነት እና ውጤታማነት የሚረጋገጠው ሁሉም የሚመለከታቸው ተቋማትና አካላት (ባለድርሻ አካላት) እጅና ጎንት ሆነው ሲሠሩ ብቻ እንደሆነ እሙን ነው፡፡በዚህ መሰረት ግብርና ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ፣ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከተማ አስተዳደር፣ የአዲስ አበባ ከተማ የተማሪዎች መጋቢ እናቶች፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሌሎች የፕሮግራሙ ደጋፊ አካላት ከወትሮው በተለየ በመናበብ እና በመቀናጀት ፕሮግራሙ እንዲሰምር በመረባረብ ላይ ይገኛሉ፡፡

በአዲስ አበባ ዙሪያ ከሚገኙ አነስተኛ ማሳ አርሶ አደሮች ጋር በግብርና ውል ስምምነት (በሽጦ ማምረት መርህ) ላይ በመመስረት በዘላቂ የገበያ ትስስር ለትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራሙ ምርቶች ሲያቀርቡ የሚከተሉት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች ይገኛሉ፡፡የኅብረት ሥራ ማህበራት አባል አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ አማራጭ ስለሚፈጠርላቸው የገበያ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፣ በግብርና ግብይት የእሴት ሰንሰለት ውስጥ የአካባቢው አርሶ አደሮች ያላቸው ሚና ስለሚያድግ አላስፈላጊ የገበያ ተዋናዮች ጣልቃ ገብነትን ይቀንሳል፡፡አነስተኛ ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮች ለትምህርት ቤት ምገባ መርሀ ግብር ጥራት ያላቸው የግብርና ምርቶችን በበቂ መጠን በማቅረብ የገበያ ፍላጎትን ማሟላት ይችላሉ፡፡

**የኅብረት ሥራ ማህበራት አባል አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ አማራጭ ስለሚፈጠርላቸው የገበያ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፣ በግብርና ግብይት የእሴት ሰንሰለት ውስጥ የአካባቢው አርሶ አደሮች ያላቸው ሚና ስለሚያድግ አላስፈላጊ የገበያ ተዋናዮች ጣልቃ ገብነትን ይቀንሳል**

እስካሁን የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን የፕሮግራሙን የፍላጎትና አቅርቦት፣ የግብርና ግብይት እና ባለድርሻ አካላትን በመስክ በመገኘት እና በሁለተኛ ደረጃነት በሰነድ የተሰበሰበውን የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መረጃን በመጠቀም ሁኔታዊ ትንተና አድርጓል፡፡ የሪፖርቱን ውጤት ለግብርና ሚኒስቴር ፣ ለአዲስ አበባ ከንቲባ ጽህፈት ቤት እንዲሁም ለተወሰኑ የክልል ባለድርሻ አካላት በማቅረብ ግብዓት ታክሎበት ዳብሯል፡፡በተጨማሪም፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር፣ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን እና የኦሮሚያ ክልልን ያቀፈ የቴክኒክ ቡድን ተዋቅሮ የተለያዩ ሰነዶችን ማለትም ረቂቅ የኮንትራት ግብርና ውል ስምምነት ሰነድ፣ እና ረቂቅ የመግባቢያ ሰነድ ውል እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

ሠሞኑን ለአንድ ቀን በተዘጋጀ አውደ-ጥናትም ከላይ የተጠቀሱት ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በትምህርት ቤቶች ምገባ ፕሮግራም እና በአነስተኛ ገበሬዎች መካከል በግብርና የውል ስምምነት ትስስር ዓላማና አተገባበር ላይ ለባለድርሻ አካላት እና ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡በተጓዳኝም በከፍተኛ አመራሩ የተዋቀረው የቴክኒክ ቡድን ያዘጋጃቸውን ልዩ ልዩ ረቂቅ ሰነዶች በአውደ ጥናቱ ላይ ለታደመው አካል እንዲቀርቡ በማድረግ ሠነዶቹን በገንቢ ግብዓቶች በማዳበር ወደ ቀጣይ የትግበራ ምዕራፍ ለመግባት አስተማማኝ መሰረት ተጥሏል፡፡በቀጣይ ጥቂት ቀናት አነስተኛ ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮችን ከፕሮግራሙ ጋር በዘላቂነት በግብይት ለማስተሳሰር የመግባቢያ ሰነድ የፊርማ ሥነ ስርዓት ይካሄዳል፡፡

የመግባቢያ ሰነዱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እየተከናወነ ላለው የትምህርት ቤት የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም ቀጣይነትና ወጥነት ያለው አፈጻጸም እንዲኖር ለማስቻል በኦሮሚያ ልዩ ዞን የሚገኙ አነስተኛ አርሶ አደሮች በውል ስምምነት ላይ የተመሰረተ የግብርና ምርት እንዲያቀርቡ የሚያደርግ ነው፡፡ስምምነቱ ቀጥተኛ የግብይት ትስስር ስርዓት የመፍጠር ዓላማ ያለው የሙከራ ፕሮጀክት ሲሆን፤ በቀጣይም ወደ ሌሎች የሀገራችን አካባቢዎች እንዲሰፋ ይደረጋል፡፡የትምህርት ቤት የተማሪዎች ምገባ መርሀ ግብር ለሀገራችን ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገራዊ ጠቀሜታ ይዘላት የመጣ ኢንቨስትመንት ነው፡፡

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et